ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት፣ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት
በያሉበት

በውጭ አገሮች ኗሪ የሆኑትን ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የአገራቸው ደጋፊ ኃይል እንዲሆኑ ለማስቻልና በተለይ ከ3ኛው አገራዊ ምርጫ ጋር ተያይዞ ስለአገራቸው ሰላም፣ ልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ትክክለኛ ግንዛቤ ኖሯቸው ከአገራቸው ጋር የጀመሩትን ትስስር ማጠናከር እንዲችሉ ለ1998 ዓ.ም. ቀሪ ጊዜ የኮንስቲትወንሲ ግንባታ መሪ-ዕቅድና ማንዋል ተዘጋጅቷል::

አዲስ ተሿሚ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደሮችና የኮንስቲትወንሲ ግንባታን የሚከታተሉ ዲፕሎማቶች ወደየምድብ ሥፍራቸው ተንቀሳቅሰው መደበኛ ሥራቸውን እስኪጀምሩ ድረስ ከወዲሁ ይህንኑ መሪ-ዕቅድ መሠረት በማድረግና ከአካባቢያችሁ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ዝርዝር ዕቅድ እንድታዘጋጁና ዕቅዱን ለመተግበር ያሉትን አመቺና ፈታኝ ሁኔታዎች ለይታችሁ እንድትቆዩ እያሳሰብን፣ መልዕክቱ በኢ-ሜይል አድራሻችሁ እንደደረሳችሁ እንድታሳውቁን እንጠይቃለን::

ከሰላምታ ጋር

ውብሸት ደምሴ /አምባሳደር/
በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን
ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር

# የ1998 ቀሪ ጊዜ የኮንስቲትወንሲ ግንባታ
# መሪ ዕቅድ

## I. መግቢያ

በተለያዩ የውጭ አገሮች በተለይም በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ተወላጆችን የልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ አጋሮቻችን አድርጎ ለማሰለፍና ትስስሩን በቀጣይነት ለማጠናከር ከ3ኛው አገርአቀፍ ምርጫ ጋር ተያይዞና ከዛም በፊት የነበረውን በተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችና ደጋፊዎች አማካይነት የሚካሄደውን ጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሠረተ ፕሮፓጋንዳና አፍራሽ ተግባር ለማጋለጥና በአሸናፊነት ለመወጣት ቁርጠኛ አሰላለፍ ይጠይቃል::

በውጭ አገሮች በሚኖረው ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለው የፖለቲካ የኃይል ሚዛን በዴሞክራሲያዊ ኃይሎች አሸናፊነት እንዲጠናቀቅና በውጭ ጠንካራ ደጋፊ ኃይል እንዲኖረን ለማስቻል በቅድሚያ በአሁኑ ወቅት በመስኩ ያለው ቁልፍ ችግር ምን እንደሆነ መለየትን ይጠይቃል::

ከዚህ አንፃር ያለው ችግር በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በመንግሥት በኩል የሚሰጡት የማበረታቻ ልዩ ልዩ ጥቅሞችና መብቶች አፈፃፀም ላይ ያለ ችግር አይደለም:: በዚህ መስክ ያለንን የአፈፃፀም ችግር ሙሉ በሙሉ ብንፈታና ከዚህም አልፈን ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞችን ብንሰጥም እንኳን በዋነኛነት በፖለቲካ አመለካከታቸው ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚፈጥር አይሆንም::

በእኛ ዕምነት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ዙሪያ ያለው ቁልፍ ችግር አክራሪ የፖለቲካ ቅኝት ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦችን አቅም ለማዳከም የሚያስችል የፖለቲካና የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን በበቂ ደረጃ መሥራት አለመቻል ነው::

በመሆኑም በቀጣዩ የ1998 ቀሪ የበጀት ዓመት ጊዜ በኮንስቲትወንሲ ግንባታ ዘርፍ ከላይ የተጠቀሰውን ቁልፍ ችግር ለመፍታት ሁለት እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ አቅጣጫዎችን በመከተል በአገር ውስጥ (በዋና መ/ቤትና) በተባባሪ አካላት ዘንድ በጋራ የሚከናወኑ ተግባራትን እንዲሁም በውጭ አገሮች በሚገኙ ሚሲዮኖቻችን የሚሠሩ ተግባራትን ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል::

በሚሲዮኖቻችን ዘንድ የሚከናወኑ ተግባራት እንዲሁም በአገር ውስጥ ይህንኑ ጥረት ለማሳካት በዋናው መ/ቤትና በሚመለከታቸው ተባባሪ አካላት ዘንድ በቀጣዮቹ ቀሪ ወራት ውስጥ ሲሠሩ የታቀዱ ተግባራት በሚቀጥሉት ሁለት ክፍሎች ቀርበዋል::

## II. የአፈጻጸም አቅጣጫ

የ1998 ቀሪ ጊዜ የኮንስቲትወንሲ ግንባታ ዕቅድ የተዘጋጀበት ዋና ዓላማ እስከአሁን በዘርፉ የተሰሩ ሥራዎችን በመገምገም በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በትውልድ አገራቸው በመካሄድ ላይ ያለውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ለማገዝና እራሳቸውንም ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ከማድረግ አኳያ ትርጉም ያለው ሥራ ባለመሥራቱና የተወሰኑ የተጀማመሩ ሥራዎች ቢኖሩም ስፋትና ቀጣይነት ያላቸው ሆነው አልተገኙም::

ስለሆነም በውጭ የሚኖሩ ወገኖች በቀጣይነት ከሥርዓቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና በሚፈልጉትና በሚችሉት ደረጃ ስርዓቱን እንዲደግፉ ለማድረግ ቀጥሎ የሠፈሩትን የአተገባበር አቅጣጫዎች እያንዳንዱ ሠራተኛ ከላይ እስከታች ተከትሎ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገሮች መ/ቤቱ ለማምጣት የፈለገውን ለውጥ እውን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል::

### 2.1 በመረጡት አጀንዳ ዙሪያ ማሰባሰብ

የኮሚዩኒቲ አባላት የሚሰባሰቡበትን አጀንዳ ራሳቸው መርጠው ካስፈለገም እኛ አማራጭ ብቻ አቅርበን በፈለጉት አጀንዳ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ ማገዝ አለብን:: ሳይሰባሰቡ የቆዩ ጀማሪዎችም ከቀላል አጀንዳ ጀምረው በየጊዜው በመመካከር ወደ ትልቅና በርካታ አጀንዳዎች እያሰፉት ሊሸጋገሩ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብን:: በተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ የተደራጁት ደግሞ በሂደት አጀንዳቸውን እያስተካከሉና እያሰፉ ወደ ላቀና ሰፋ ወዳለ አጀንዳ እንዲሸጋገሩ ማበረታታት አለብን:: በዚህ መልኩ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በመሰባሰባቸው ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸውን አጀንዳዎች ቀላልና አወዛጋቢ ካልሆኑት በመጀመር ወደ ከፍተኛ መሰባሰቢያ አጀንዳ በሚያሸጋግር መልኩ እንደቅደም ተከተሉ እንደሚከተለው ቀርቧል::

ሀ. የማህበረሰቡን አባላት መብትና ጥቅም በሚያስከብሩ በተለይም ገንዘብ ለቤተሰብ በማስተላለፍ፣ ቤት በመስራትና በኢንቨስትመንት ተሳትፎ፣ ባሉበት ሀገር መብታቸውን በማስከበርና ተገቢ አገልግሎት በማግኘት ዙሪያ፣

ለ. በትውልድ ወረዳቸው፣ ከተማቸው፣ የድሮ ትምህርት ቤታቸው፣ ክልላቸው ለሚሰሩ የልማት ሥራዎች በገንዘብና በዓይነት መዋጮ በማበርከት ዙሪያ፣

ሐ. በሙያቸው ተደራጅተው በእውቀትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዕገዛ ዙሪያ፣

መ. በሚያምኑበት ውስን ፖሊሲ ዙሪያ /የገጠር ልማት፣ የከተማ ልማት፣ የጤና፣ የትምህርት ወዘተ./፣

ረ. ሕገ-መንግሥቱን ደግፎ በመሥራት ዙሪያ፣

ሰ. መሠረታዊ የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፖሊሲዎችን ደግፎ በመሥራት ዙሪያ፣

2.2 በመረጡት የአደረጃጀት አግባብ እንዲደራጁ ማገዝ

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውን በመረጡት አደረጃጀት ዙሪያ እንዲደረጁ ለማገዝ ታሳቢ መሆን የሚገባቸው ጉዳዮች፣

- በሙያ፣ በፆታ፣ በባህል፣በእምነት፣ ...ወዘተ በቡድን ወይም በማህበር
- በልማት ረገድ፡- በቱሪዝም፣ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በአካባቢ ጥበቃና ልማት፣ ሰብዓዊ ዕርዳታና ድጋፍ፣ ወ.ዘ.ተ.
- በብሄር፣ ብሄረሰብ መብት ዙሪያ፣
- በዲፕሎማሲና የገጽታ ግንባታ፣
- በጥናትና ምርምር ማኅበር ወይም ቡድን፣
- በድረ-ገጽ፣ የሚዲያ ሥራ /ጋዜጣ፣ ሬዲዩ፣ ቲቪ ወዘተ/

2.3 የኮሚዮኒቲ አባላት በተደራጁበት አግባብና አጀንዳ ዙሪያ ለውጥ ሲኖር ፍላጐታቸውንና ወቅታዊ ሁኔታውን በማየት እገዛ ማድረግ፣ በውጭ የሚኖረው የኮሚኒቲ አባል ሕይወት ተለዋዋጭና ቀጣይ በመሆኑ ይህንኑ dynamics ተገንዝቦ በቋሚነት ከሚከናወን ወጥ አደራጀጃትና የማይቀየር ደረቅ አጀንዳ መታቀብ ያስፈልጋል:: ስለሆነም አጀንዳቸውና አደረጃጀታቸው እንደ ፍላጐታቸውና ወቅታዊ ሁኔታ ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲያድግና የተለያዩ አማራጮችን እንዲያካትት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅብናል::

2.4 በውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንን በመረጡት አጀንዳና አደረጃጀት ዙሪያ እንዲሰባሰቡ በማድረግ በቀጣይነት ጥቅሞቻቸው እየተከበረ ተሳትፎዋቸው እንዲጠናከር ይደረጋል:: በአገር ውስጥና በውጭ አገሮች የሚኖራቸው መብትና ጥቅም እንዲረጋገጥ፣ ወደ አገር ቤት እንደልብ እንዲመላለሱ፣ ንብረት በሕጋዊ መንገድ እንዲያስገቡና ቤት እንዲሰሩ፣ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፣ ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ እንዲያስተላልፉና የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ፣ የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ እንዲያገኙ ማገዝና በዚህ ዙሪያ የሚከሰቱ እንቅፋቶችን ለመፍታት ከነሱ ጋር አብረን መንቀሳቀስ ይኖርብናል::

2.5 በዚህ ዕቅድ ውስጥ በውጭ የሚኖሩ የኮሚዩኒቲ አባላት በመረጡት አጀንዳና በፈለጉት አደረጃጀት ዙሪያ ተሳትፎዋቸውን ለማጠናከርና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሰፈሩ ጉዳዮች አተገባበር ቅደም ተከተል በአሁኑ ወቅት የጥቂት ተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት የተከተሉትን አፍራሽ አቅጣጫና በየአህጉሩ እየመሠረቱት ያለውን የግንኙነት መረብ/Network/ ሊመክትና በሂደትም ሊያከሽፍ በሚችል አግባብ መሆን ይገባዋል:: ከዚህም አንፃር በዕቅዱ ውስጥ በውጭ አገሮችም ሆነ በአገር ውስጥ የሚከናወኑ ጥናቶች ለብቻቸው ተነጥለው የሚሠሩ ሳይሆን የኮሚኒቲ አባላትን እያሰባሰብን፣ መረጃ እየሰጠንና እያደራጀን ጎን ለጎን የምንተገብረው ይሆናል::

III. በውጭ አገሮች የኮንስቲትወንሲ ግንባታን ከማሳካት አኳያ የሚከናወኑ ተግባራት፣

3.1 በሚሲዮኖች የሚከናወኑ ተግባራት

3.1.1 በውጭ አገሮች ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መካከል ለስርዓቱ ደጋፊ የሆኑ ኃይሎችን ለማፍራትና ለማጠናከር የሚረዳ የጥናት ስራ ማካሄድ፣

ዓላማ:-

አገራችን በውጭ አገሮች ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር የሚኖራትን ግንኙነት በተጨባጭ መረጃ ላይ በመመስረት ተጠቃሚነታቸውንና ተሳትፏቸውን ውጤታማ ማድረግ፣

ግብ:-

በውጭ አገሮች ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ውስጥ ሙሉ በሙሉ በውስን ጉዳዮች ዙሪያ ከሥርዓታችን ጎን የሚሰለፉትን ለይቶ ማወቅና አደራጅቶ ማንቀሳቀስ ይጀመራል::

ዋና ዋና ተግባራት:-

- ሚሲዮኖች ባሉበትና በሚሸፍኗቸው አገሮች ተደራጅተው ስለሚገኙ ማኅበራትና ስብስቦች ተጨባጭ መረጃ ማሰባሰብ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣

  የጥናቱ ትኩረት:-

  - ስለአደረጃጀታቸው ዓላማ፣

- በሬዲዮ፣ በጋዜጣ፣ በቴሌቪዥን፣ በድረ-ገፅ የሚሰሩ ሥራዎች ይዘትና አቀራረብ ላይ ያሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው፣
- የስብሰባ፣ የደብዳቤ መልስ አሰጣጥ፣ በአካል የማነጋገር፣ የሥልክ፣ ፋክስና ኢ-ሜይል ግንኙነት ችግሮቻችንና አፈታቱ፣

- በተለያዩ ኮሚኒቲዎች ተሰሚነት ያላቸው፣ በተለያየ መንገድ ሲሳተፉና ሲደግፉ የቆዩ እንዲሁም መሳተፍ የሚፈልጉ ቅን (positive) ሰዎች የመለየት ጥናት:-
  - የጥናቱ ትኩረት እስከ አሁን ያከናወኑትን ሥራ በማጥናትና ፍላጐታቸውን በመጠየቅ፣
  - ተልዕኮም በመስጠትና ውጭ ሀገር ያሉ ከእኛ ጋር የተሰለፉ ወገኖች ከሚሰጡት ጥቆማ በመነሳት፣
  - ሃገር ቤት ካሉ ቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው እንዲሁም በተለያየ መንገድ የሚያውቋቸው ሰዎች እንዲጠቁሙና እንዲያገናኙ በማድረግ፣
  - ሃገር ቤት ያሉ የገገር ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች የሚያውቋቸውን በውጭ ነዋሪ ቤተሰቦቻቸውንና የቅርብ ጓደኞቻቸውን እንዲጠቁሙ በማድረግ፣
  - ሃገር ቤት ተመልሰው የገቡ ውጭ ሃገር የነበሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የሚያውቋቸውን እንዲጠቁሙ በማድረግ፣

- ለእያንዳንዱ ጥናት መጠይቅ፣ መለስተኛ ጥናታዊ መድረኮችና አጥኚዎች ተለይተው እየተዘጋጁለት ይካሄዳል፣
- በየብሔሩ ተወላጆች ላይ የሚካሄደው ጥናት ተለይቶ ራሱን ችሎ ይካሄዳል፣

የሚጠበቀው ውጤት:-
በውጭ አገሮች ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በቂና የወደፊት የትስስር አቅጣጫን ሊደግፍ የሚያስችል መረጃ ይኖራል::

የክንውን ጊዜ:-
ሚያዝያ - ሰኔ 1998 ዓ.ም.

- ስለአደረጃጀታቸው ይዘት/የብሔር፣ የሙያ፣ ትውልድ ቦታ፣ የማኅበር ወይም የቡድን ወ.ዘ.ተ/
- የአባላት ብዛት ግምት
- ጥቅማቸውን በማረጋገጥ ዙሪያ ስላለ ችግርና ስለሚፈልጉት እገዛ፣
- ተሳትፎ ለማድረግ ስላለባቸው ችግርና የመፍትሄ ሃሣብ፣
- እስካሁን ስላከናወኗቸው አበይት ተግባራት ይሆናል::

- ያልተደራጁ ደጋፊና ገለልተኛ ኃይሎችን በሚመለከት ተጨባጭ መረጃ ማሰባሰብ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣

  የጥናቱ ትኩረት:-

  - ጥቅማቸውን ከማስከበር አንጻር በሀገር ቤትና ባሉበት ሊሠሯቸው ስለሚፈልጓቸው ተግባራት ምንነት፣ ስለችግራቸውና ስለሚፈልጉት እገዛ፣
  - ተሳትፏቸው በምን መስክ ቢሆን እንደሚመርጡ/ በሙያ፣ በጽሑፍ፣ በሰልፍ፣ በዲፕሎማሲ፣ በፋይናንስ ወዘተ/
  - በምን ዓይነት አደረጃጀት ሊሳተፉ እንደሚፈልጉ/በግል፣ በቡድን፣ በማኅበር . . . ወዘተ/
  - ማንን ከጐናቸው ማሰባሰብና ማሰለፍ እንደሚችሉና ምን እገዛ እንደሚፈልጉ ይሆናል::

- በጥቅሞቻቸው ዙሪያ የተሻለ የመፍትሄ አቅጣጫን የሚጠቁም ጥናት ማካሄድ፣
- የጥናቱ ትኩረት:-

  - ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ያለ ችግር፣
  - ቤት ለመሥራት ያለ ችግር፣
  - የትውልድ ኢትዮጵያዊነት ካርድ የመጠቀም ችግር፣
  - ኢንቨስት ለማድረግ ያለ ችግር፣
  - የውጭ ምንዛሪ በሀገር ቤት ባንክ ለማስቀመጥ ያለ ችግር፣
  - የስደተኛ መብት በማስከበር ዙሪያ ያለ ችግር ይሆናል::

- ለኮሚኒቲው መልዕክት የምናደርስባቸው የሚዲያና የግንኙነት አግባቦች ላይ ያሉ ችግሮችን፣

  የጥናቱ ትኩረት:-

### 3.1.2. የግንኙነትና የአደረጃጀት ጥናት

ዓላማ:-

ሚሲዮኖች ከኮሚዩኒቲ አባላት ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነትና የኮሚኒቲ ሥራ አደረጃጀት ሥርዓት ለመዘርጋት፣

ግ ብ:-

ሚሲዮኖች በተወከሉበትና በሚሸፍኗቸው አገሮች ካሉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጋር የሚኖራቸው የግንኙነትና የሥራ አደረጃጀት ሥርዓት ይቀየሳል::

ዋና ዋና ተግባራት:-

- ሚሲዮኖች ከራሳቸው ሠራተኛ ጀምሮ በየከተማው ነዋሪ ከሆኑ የኮሚኒቲ አባላት ጋር የሚኖራቸውን የግንኙነት ሥርዓት በኢ-ሜይል፣ በሥልክ፣ በፋክስ ብቻ ሳይሆን በተደራጀና ባልተደራጀ ጠንካራ አንቀሳቃሽ ኮር በኩል የሚኖር የግንኙነት ሥርዓት ለመፍጠር የሚያስችል አካሄድ ማጥናት፣
- ይህን በአንድ አካባቢ የተለየ ኮሚኒቲ ለማንቀሳቀስ የኤምባሲ ሠራተኞችም ሆነ ሌላው የሥርዓቱ ደጋፊ በግልና በጋራ እንዴት ተደራጅቶ ሥራውን መምራት እንደሚችል ማጥናት፣
- በዚህ አሠራር ዙሪያ ጠንካራ የኮምዩኒቲ አባላትን ሃሳብ ማሰባሰብ፣ የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ መውሰድ፣
- በጥናቱ ውጤቶች መነሻ በሚሲዮኖች ያለውን የሰው ኃይል ብቃቱን ለይቶ ከጠንካራ የኮሚኒቲ ኮር ጋር አስተሳስሮ ማንቀሳቀስ፣

የሚጠበቅ ውጤት:-

በሚሲዮኖች ዘንድ ለኮንስቲትወንሲ ግንባታ አመቺ የሆነ የሥራ አደረጃጀት ሥርዓት ተቀይሷል::

የክንውን ጊዜ:-

ከሚያዝያ - ሰኔ 1998

### 3.1.3. ከዲያስፖራ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዘው የሚከናወኑ ተግባራት

ዓላማ:-

ከ3ኛ አገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ በውጭ አገሮች ነዋሪ የሆኑትን ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ተወላጆች በጥቂት ተቃዋሚ ኃይሎች አፍራሽ ፕሮፖጋንዳና የተለያዩ ማስፈራሪያ ሥልቶች ተቋርጦ ያለውን ግንኙነትና መገለል አቅጣጫ ለመለወጥ የሚያስችል የፖለቲካ ሥራ በመሥራት በአገሩ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ላይ ዕምነት እንዲያሳድር ማድረግ፣

ግ ብ:-

በውጭ ነዋሪ የሆነው አብዛኛው ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ተወላጅ በአገሩ ያለውን የዴሞክራሲያዊ ግንባታ ትክክለኛ ሂደት መገንዘብ የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎች ማመቻቸት ተችሏል።

ዋና ዋና ተግባራት:-

- የአክራሪውን የተቃዋሚ ጐራ ለማዳከም እንዲረዳ በውጭ አገሮች ያሉ ቀንደኛ አስተባባሪ የሆኑ አባላትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለዋናው መ/ቤት ማስተላለፍ፣
- ከዋናው መ/ቤት በሚደርሳቸው የእነዚህ አክራሪዎች የተለያየ መረጃ /በዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በገንዘብ ዝርፊያ፣ በመንግሥትና በሕዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት አላግባብ ተጠቅመው የከበለሉትን፣ ወዘተ/ ለአብዛኛው የኮሚኒቲ አባላት ማጋለጥ የሚያስችል የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሥራት፣
- ከእነዚህ መካከል በዘር ማጥፋትና የሕዝብና የመንግሥት ንብረት በመዝረፍ የተሳተፉትን መሪ-ተዋንያን በሕግ ለመጠየቅ የሚያስችል የተጠናከረ እንቅስቃሴ በማካሄድ ተጠያቂዎቹን ለፍርድ ማቅረብ፣
- አክራሪ ተቃዋሚዎች ከሚኖሩባቸው አገሮች መንግሥታት ጋር በዲፕሎማሲያዊ መስመር በመገናኘት የአገራችንን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ እንቅስቃሴዎችን በየአገሮቻቸው እንዲካሄድ መፍቀድ እንደሌለባቸው የተለያዩ የሕግ፣ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ነጥቦችን በማንሳት በጋራ መተባበር የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች መፍጠር፣ ከዚህም አንፃር:-
    - የአክራሪ ተቃዋሚዎቹ መሪዎች የሚኖሩባቸውን አገሮች ዜግነት የወሰዱ ስለሆነ በእኛ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደሌለባቸው የእነሱንም ሆነ የአገራችንን ሕጎች በመጥቀስ ማስረዳት፣

- አክራሪ ተቃዋሚዎቹ የተለያየ ሕገ-ወጥ የማስፈራሪያ መንገዶችን በመጠቀም ንፁሃን ዜጎች በሰላም የሚኖሩበትንና የፈለጉትን የፖለቲካ አቋም እንዳያራምዱ ተፅዕኖ የሚያደርጉና የአገሮቹን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች የሚጥሱ መሆናቸውን ማሳየት፣
- በየአገሮቹ መንግሥታት በጀት የሚንቀሳቀሱ የሬዲዮ ጣቢያዎችን ለጠባብ የፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃነት ድጋፍ በመስጠት የአገራችንን ሰላምና መረጋጋት የሚያውኩ ቅስቀሳዎችን እንደሚያካሂዱና በአገሮቻችን መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት የማያንፀባርቅ ፕሮግራም እንደሚያሠራጩ በተጨባጭ ማስረጃዎች አስደግፎ ማብራራት፣
- ጥገኝነት ጠይቀው በየአገሩ ያሉና ለተቃዋሚ ድርጅቶች መሣሪያ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ከሚኖሩባቸው ከተሞች ርቀው መሄድ ስለማይፈቀድላቸው ይህንኑ ለየአገሩ የፖሊስና የአስተዳደር አካላት በማሳወቅ እንቅስቃሴያቸው እንዲገደብ ማድረግ፣

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከመንግሥታቱ ጋር በትብብር ለመንቀሳቀስ የሚያስችል መግባባት ከሚመለከታቸው የመንግሥታቱ አካላት ጋር መፍጠር፣

የሚጠበቀው ውጤት:-

በምዕራብ አውሮፓና አሜሪካ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ተወላጅ የጥቂት አክራሪ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራር አባላትና ደጋፊዎች ማንነትና አፍራሽ ተልዕኮ ተገንዝበዋል::

የክንውን ጊዜ:-

ከመጋቢት 15 - ሰኔ 30/1998 ዓ.ም.

3.1.4. ደጋፊ ኃይሎችን ከማጠናከርና ተሳትፏቸውን ከማስፋት አኳያ የሚከናወኑ ተግባራት

ዓላማ:-

የደጋፊ ኃይሎችን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚያስችሉ የፖለቲካና የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን መሥራት፣

ግ ብ:-

ሚሲዮኖቻችን በተወከሉባቸውና በሚሸፍኗቸው አገሮች የሚገኙ ደጋፊ የኮምዩኒቲ አባላትንና ስብስቦችን መረጃና ድጋፍ በመስጠት ከነበሩበት ጠባብ አካባቢ ወጥተው ሌሎች ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንን ለማነሳሳት መንቀሳቀስ ጀምረዋል::

ዋናዋና ተግባራት:-

ሀ. ተደራጅተው የሚገኙትን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚሰሩ:-

- የወቅቱን የተቃዋሚ ኃይሎችን አፍራሽ እንቅስቃሴ በመቃወም በተለያየ መልኩ የተደራጁና የአገራችንን ትክክለኛ የፖለቲካ ገፅታ በማንፀባረቅ ሎቢ የሚያደርጉ ግለሰቦችንና ስብስቦችን በመረጃና የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠት ማጠናከር፣ በቀጣይ ተሳትፏቸውን ሊያጎለብት የሚያስችል ዕቅድ ከእነሱ ጋር በመመካከር ማውጣት፣
- በአገራችን የፌዴራል የፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ በአጋርነት የቆሙ ክልሎች ብሔር-ብሔረሰብ ተወላጆችን /የሶማሌ፣ ሐረሪ፣ ጋምቤላ፣ አፋር ወዘተ./ ስብስብ በመረጃ መደገፍ፣ የእንቅስቃሴ አቅጣጫዎችን በማመላከት ባሉበት አገር የትውልድ አገራቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ጥብቅና እንዲቆሙ /advocacy/ ማድረግ፣
- የእነዚህን አጋር ማህበረሰብ ተሞክሮ ተጠቅሞ ደረጃ በደረጃ የሌሎች ትላልቅ ብሔር ተወላጆችን ስብስቦች በየተደራጁበት ለስርዓቱ በጎ አመለካከት ያላቸው አመራሮችና አባላት እንዲኖራቸው የሚያስችል እገዛ በመስጠት የደጋፊ ኃይሉን መሠረት ማስፋት፣
- የተነጣጠሉና በየአገሩ የተሰራጩ አደረጃጀቶች አጋርነት ፈጥረው በከተማ፣ በክልልና በሀገር ደረጃ የጋራ አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የተለያዩ የልማት፣ የሙያ ማህበራትንና ወጣቱን ትውልድ ከአገራችን ዘላቂ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ አጀንዳ አንፃር ማሰባሰብና የአገራቸውን ዕድገት ሲደግፉና ይህንን የሚቃወሙትንም ለመመከት እንዲችሉ ተሳትፏቸውን በመረጃና በተለያዩ ድጋፎች ማጠናከር (በስብሰባ፣ በልዩ ልዩ ሚዲያ፣ በድረ-ገጽ ወዘተ)፣

ለ. ያልተደራጁና በገለልተኝነት የቆሙትንና በተቃዋሚ ኃይሎች ተወናብደው የሚገኙትን ወደ ደጋፊነት ለማምጣት የሚሰሩ ስራዎች:-

- በአነስተኛ አጀንዳና በመለስተኛ አደረጃጀት እንደፍላጎታቸው መሳተፍ እንዲችሉ የማግባባት ስራ መስራት፣ ማደራጀት፣

* ግልፅ መውጣት የማይፈልጉትንም በግልና በቡድን በሕቡእ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማግባባትና፣ ማሰማራት፣
* ሰፊ ትስስርና ተሰሚነት ያላቸውን የኮሚዩኒቲ አባላት በመጠቀም በጎ አመለካከትና ውስን ተሳትፎ የነበራቸውን በቅድሚያ ማንቀሳቀስ፣ ሌሎቹን እንዲያግባቡ ማሰማራት፣
* በየአገሩ ያሉትን ደጋፊ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ ድረ-ገጾችና የሚዲያ ተቋማትን በተጨባጭ መረጃ በመደገፍ፣ ከእነዚህም ጋር የተቀናጀ የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን በመሥራት፣ በአመለካከት ረገድ የተገኘውን ውጤት በየጊዜው በመገምገምና የታዳሚውን አስተያየት በማሰባሰብ ቀጣይነት ባለው መልኩ መንቀሳቀስ፣
* ከየአገሩ የተውጣጡ ተሰሚነት ያላቸው ኢትዮጵያዊያንን እየመረጡ ወደ አገር ቤት አስመጥቶ በመመካከር ግንዛቤ ጨብጠው በመመለስ የተቀረውን ማህበረሰብ አመለካከት እንዲቀይሩ ማሰማራት፣ ለዚህም አመቺ መድረኮችን በየወቅቱ ማዘጋጀት፣
* እነዚህን ተግባራት ለማስተባበር የሚችል የተጠናከረ መዋቅርና የአመለካከት ችግሮችን ሊያስተካክል የሚችል አሠራር በሚሲዮኖቻችን ዘንድ ፈትሾ ተግባራዊ ማድረግ፣ በየአገሩ ያለውን ማህበረሰብ በወረዳ /district/ ደረጃ ወይም አመቺ በሆነ አወቃቀር በመከፋፈል ከኮምዩኒቲ አባላት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ማመቻቸትና የማህደር ማሰባሰብ ሥራ መሥራት፣ /ለመነሻ ያህል የደቡብ አፍሪካን የwarden system ተሞክሮ መጠቀም/፣

የሚጠበቀው ውጤት:-

የአገራችን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረው በውጭ ያለው ደጋፊ ኃይል ተጨባጭ አስተዋጽኦ ማድረግ ጀምሯል::

የክንውን ወቅት:-

ከመጋቢት 15 - ሰኔ 30/1998 ዓ.ም.

### 3.1.5. የልማት ኃይሎችን ከማጠናከር አኳያ የሚከናወኑ ተግባራት

ዓላማ:-

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን ስልማት ሥራ አስተባብሮ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲያችን አጋዥ ኃይል እንዲሆኑ ማስቻል፣

ግ ብ:-

በውጭ ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን መካከል በመደራጀትም ሆነ ሳይደራጁ ከመንግሥት ጎን ቆመው በልማቱ በመሳተፍ በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በሚገኙ ኩባንያዎችና በአገራችን መካከል እንደ ድልድይ በማገልገል ለወጪ ምርቶቻችን ገበያን በማፈላለግ፣ ኢንቨስተሮችን በመመልመል ራሳቸውንና አገራቸውን የሚጠቀሙበት ሁኔታ ተመቻችቷል፣

ዋና ዋና ተግባራት:-

- በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ውስጥ በጎ አመለካከትና ፍላጎት ያላቸው ሁሉ ለአገራችን የወጪ ምርቶች አዳዲስ ገበያ ለማስገኘት፣ ምርቶችን ለማሻሻጥ፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመመልመል፣ ከውጭ ባለሃብቶች ጋር ሽርክና በመፍጠርም ሆነ ራሳቸውን ችለው በአገራቸው ኢንቨስት ለማድረግ በተጨባጭ እንዲነሳሱ መገፋፋትና ዕገዛ ማድረግ፣

- ከክልል መስተዳድሮች ጋር በመቀናጀት ተጨባጭ የሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን በማሰባሰብ ለተደራጁት ደጋፊ ማህበራት መስጠት፣

- በውጭ የተቋቋሙ የኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የንግድ ድርጅቶችና የቱሪዝም ማስፋፊያ ማዕከላትን target በማድረግ ፍላጎታቸውን ማሟላትና ችግሮቻቸውን በጋራ ለመቅረፍ መንቀሳቀስ፣

- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ወደ አገር ቤት በሕጋዊ መንገድ የሚልኩት ገንዘብ መጠን እንዲጨምር እስከ አሁን ያለውን አካሄድ ገምግሞና ደካማ ጎኖችን ለይቶ መፍትሄ በማስቀመጥ የተቀላጠፈ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

- በዚህም ሂደት በአገር ቤት በውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ለመክፈት መሰናክል የሆኑ ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለይቶና የሌሎች አገሮችን ተጨባጭ ልምዶች ቀምሮ ከዋናው መ/ቤት ጋር በመሆን አፈፃፀሙ ውጤታማ እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፣

- በአገራችን ለሚካሄደው ልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ የሚውል ተጨማሪ resource በማስገኘቱ ረገድ አስተዋጽኦ የሚኖራቸውን ተወላጆች ለይቶ ማሳተፍ፣

የሚጠበቀው ውጤት:-
በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከመንግሥታችን ጐን ተሰልፈው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እራሳቸውን ተጠቃሚ በማድረግ አገራችን ከወጪ ንግድና ከቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በቀጣይነት እያደገ የሚሄድ ጠቀሜታን አግኝታለች፤ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱም መጠን ትርጉም ያለው ዕድገት አሳይቷል።

የክንውን ጊዜ:-
ከሚያዝያ - ሰኔ 1998 ዓ.ም.

3.1.6. ለኮሚዩኒቲ አባላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ከማሻሻል አኳያ የሚከናወኑ ተግባራት

ዓላማ:-
በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ከሚሲዮኖቻችን ቀልጣፋ፣ ግልፅና ፍትሃዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣

ግ ብ:-
የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችና አፈታቱ ተጠንቶ ወደ ማሻሻያ ሥራ ትግበራ መግባት ይጀመራል፣

ዋና ዋና ተግባራት:-

- በእያንዳንዱ ሚሲዮን የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች በQuick Wins ማሻሻያ ተፈትሸው በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ጊዜና ፍላጎት ባጣጣመ መልኩ ውጤቶቹ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በማድረግ ወደ ትግበራ መግባት፣
- ለአሠራር አመቺ ሳልሆኑ አገልግሎቶች ለምሣሌ የኢትዮጵያ የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ለመውሰድና የባንክ ሂሣብ ለመክፈት በግንባር መገናኘትን የሚጠይቁ አገልግሎቶችን ወደ ተጠቃሚው ለማድረስ የተንቀሳቃሽ ቆንስላ አገልግሎትና ሌሎች አማራጮችን በማጥናት ውጤቶቹን ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኢትዮጵያዊያን ላይ የሚደርሱ የተለያዩ በደሎች አቅም በፈቀደ መጠን ሕጋዊ መስመሩን ተከትለው ተገቢውን ፍትህ እንዲያገኙ ለማድረግ የችግሮቹን መንስዔዎች በማጥናት ግልፅ መፍትሄዎች አስቀምጦ በንቃት መንቀሳቀስ፣ /በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ላሉ ወገኖች ትኩረት መስጠት፣/

የሚጠበቀው ውጤት:-
በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሚሲዮኖች በሚሰጡት አገልግሎት ረክተዋል::

የክንውን ጊዜ:-
ከመጋቢት 15 - ሰኔ 30/1998 ዓ.ም.

### 3.2. በአገር ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ዕቅድ

በውጭ አገሮች በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ በመሠረታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ አመለካከት ለመፍጠርና ለአገራቸው የልማትና ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ ቁልፉ ሥራ በአገራችን ውስጥ በዚህ ረገድ የሚመዘገበው ዕድገትና የሚመጣው ለውጥ ነው::

ስለሆነም በአገራችን ውስጥ የዴሞክራሲ ተቋማትንና መሠረተ ልማቶችን በመገንባት፣ የብሔር-ብሔረሰቦችን መብቶችና ጥቅሞች ከማስከበር አኳያ የተከናወኑና የሚከናወኑ ተግባራትን ይህም በሕዝቡ ሕይወት መሻሻል ረገድ የሚኖረውን እንድምታ በሚያሳይ መልኩ የሚከናወኑ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራዎችና ተዛማጅ ተግባራት በሁለት ክፍሎች ተለይቶ ቀርቧል::

#### 3.2.1. ሥራውን የሚመሩ የሀገር ውስጥ አካላት አደጃጀትና የተቀናጀ አሠራር

የኮሚኒቲ ሥራ ፓኬጅን ማሳካት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ አራት ገፅታዎች አሉት:: በውጭ ሚሲዮኖች የሚፈፀሙ ሁለት ሥራዎች ሲሆኑ እነሱም የሚሲዮኖች አመራሮችና ሠራተኞች የሥራውን አቅጣጫ ጨብጠው በልዩ ትኩረት ሊፈፅሙት የሚያስችል አመለካከት መቅረፅና ብቁ ስታፍ መድቦ ከኮሚኒቲዎች ጋር እስከ እያንዳንዱ ከተማ ስብስብ ግለሰብ ድረስ የሚያስተሳስር የአደረጃጀትና የግንኙነት ሥርዓት መፍጠር ነው:: ይህ ሥራ እንዴት እንደሚጠናና ወደ ተግባር እንደሚሸጋገር ቀደም ብሎ ተገልጾአል::

በሀገር ውስጥ የሚፈፀም ሥራን የሚያሳካ የአቅም ግንባታ ሥራ ደግሞ ሁለት ገፅታዎች አሉት:: አንዱ በፌዴራል ደረጃ ሥራውን የሚያስተባብር አካል ማደራጀትና የእያንዳንዱን አካል ድርሻ መለየት ሲሆን በየክልሉ ለዚህ ሥራ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን ለይቶ የጋራ ኮሚቴ በየክልሉ በማደራጀት ምሁራን፣ ባለሃብቱንና ሽማግሌዎችን ማሳተፍ ሁለተኛው ነው::

ዓላማ:-

በውጭ አገሮች ለሚካሄደው የኮንስቲትወንሲ ግንባታ ሥራ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን ተቋማት አደረጃጀትና የግንኙነት ሥርዓት ግልፅ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ፣

ግ ብ:-

በፌዴራልና በክልል ደረጃ የኮንስቲትወንሲ ሥራን የሚያግዙ አካላት ተደራጅተውና ግልፅ የሥራ ድርሻና ግንዛቤ ይዘው መንቀሳቀስ ይጀምራሉ::

ዋና ዋና ተግባራት:-

- በፌዴራል ደረጃ በውጭ ጉዳይ መ/ቤት መሪነት የኮንስቲትወንሲ ግንባታ ሥራን የሚያስተባብርና ሌሎች ሚና ያላቸውን መ/ቤቶች ያካተተ አካል ማደራጀትና የሥራ መመሪያ ማዘጋጀት፣
- በክልሎች ደረጃ ሚና ያላቸው አካላት ተለይተው የጋራ ኮሚቴ እንዲመሠርቱና የሥራ መመሪያ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣
- በውጭ የሚኖረውን ማህበረሰብ በማሳተፍ ረገድ ያሉ ችግሮችን በቀጣይ ሊፈታና ከተባባሪ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት የሚያስችል አሠራር ከፌዴራልና ከክልል ኮሚቴዎች ጋር መቀየስ፣ የእያንዳንዱን ተባባሪ አካል የሥራ ድርሻ በግልፅ ዘርዝሮ ማስቀመጥ፣
- በውጭ ስለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ፍላጎትና ለአገራችን ሰላም ልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ያላቸውን ጉልህ አስተዋጽኦ ለተባባሪ አካላት አመራሮችና ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

የሚጠበቀው ውጤት:-

በውጭ የሚከናወነውን የኮንስቲትወንሲ ግንባታ ለማሳካት የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር በፌደራልና በክልሎች ደረጃ ተዋቅሮ ተጨባጭ ሥራ ተጀምሯል::

የክንውን ጊዜ:-

ከመጋቢት - ሰኔ 1998

### 3.2.2 ሕዝቡ ውጭ ሃገር ያሉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያንን ለማሳተፍ ሚናውን እንዲጫወት ማስተባበር

በሁሉም ክልሎች ካለው ሕዝብ ይብዛም ይነስ የተወሰኑ የየአካባቢው ተወላጆች በተለያዩ ምክንያቶች ከአገራቸው ወጥተው ኑሮዋቸውን በውጭ አገሮች መሥርተው ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ቁጥራቸው ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሆኑ በውጭ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ለአገራቸው ሰላም፣ ልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሳካት ያላቸውን ዕምቅ አቅምና የግንኙነት መረብ በተሻለ ደረጃ ወደ ተጨባጭ አስተዋጽኦ ለማሸጋገር በየክልሉ የሚኖረውን ሕብረተሰብ በተለያየ መልኩ በማሳተፍ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ዓላማ፡-

በውጭ አገር ነዋሪ የሆነው ማህበረሰብ በአገሩ ልማትና ዕድገት ሂደት ውስጥ በመሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ሕዝቡ ሚናውን እንዲጫወት ማስተባበር፣

ግብ፡-

ሕዝቡ ውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያንን በአገራቸው ሰላም፣ ልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ በመሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ጀምሯል፡፡

ዋና ዋና ተግባራት፡-

- የታዳጊ ክልሎች መስተዳድሮችና ገገር ፓርቲዎች፣ ሕዝቡን በማስተባበርና ድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ ዕቅድ ነድፈውና ፈፃሚ አካል ለይተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማስተባበር፣
- የታዳጊ ክልሎች ገሣ መሪዎች፣ ሽማግሌዎችና ምሁራን የየአካባቢያቸውን ሕብረተሰብ በማስረዳትና በማሳመን የግንኙነቱን መሠረት እንዲጥሉና ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ ማስተባበር፣
- በቤተሰብ፣ በጓደኛነት፣ በትውውቅ ደረጃ በአገር ውስጥ ሰላምን ልማትንና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ለማሳካት የሚደረጉ ጥረቶችን፣ የተገኙ ውጤቶችን ወደፊት የታቀዱ ትልሞችን በተለያዩ የመገናኛ መስመሮች በማስረዳት፣ በማግባባት፣ በመጋበዝና በማስጎብኘት የሥርዓቱ ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ ለማሳመን አብሮ መሥራት፣

- በዓበይት ክልሎችም በምሁራን፣ በነጋዴዎች፣ በታዋቂ ግለሰቦችና ማህበሮቻቸው በኩል ውጭ አገር ያሉትን ወገኖች የማሳተፍ ሰፊና የተደራጀ ሥራ እንዲሠራ በክልል መስተዳድሮችና ገገር ፓርቲዎች ዕቀድ ወጥቶ ተግባራዊ እንዲሆን ማስተባበር፣
- በክልሎች በኩል የሚሰባሰበ መሠረታዊ መረጃዎችን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዳታ-ባንክ ፈጥሮ በማደራጀትና የመረጃ ልውውጡን በማቀላጠፍ ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ አብሮ መሥራት፣

የሚጠበቀው ውጤት:-

ክልሎች በውጭ ነዋሪ የሆነውን ማህበረሰብ በመገናኘት የማስረዳት፣ የማግባባትና የመጋበዝ ሥራ ጀምረዋል::

የክንውን ጊዜ:-

ከመጋቢት - ሰኔ 1998

### 3.2.3. በፐብሊክ ዲፕሎማሲና የሕዝብ ግንኙነት መስክ የሚከናወኑ ተግባራት

ዓላማ:-

በአገር ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በልማት መስክ የሚደረጉ ጥረቶችን ከመንግሥት ራዕይ፣ ተልዕኮና ግቦች አንፃር በመቃኘት አንድ አገራዊ አመለካከት ለመፍጠር የሚደረገው እንቅስቃሴ ከአገር ውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በቀጥታ እንዲደርስ ማድረግ፣

ግ ብ:-

መንግሥትና ሕዝብ በአንድ ልብና ሃሳብ ዴሞክራሲያችን መሠረት እንዲይዝ በማድረጉና ልማቱን በማረጋገጡ ረገድ ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ በማስቻል በውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ ዕምቅ ሃብት ለዚሁ ዓላማ ግብዓት እንዲሆን ማድረግ ላይ ጉልህ ውጤት ተገኝቷል::

ዋና ዋና ተግባራት:-

- የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ሥርጭታቸውንና የይዘ ቸውን አድማስ በማሻሻል ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በብዛት በሚኖሩባቸው የዓለም ክፍሎች በቀጥታ first hand information ከምንጩ እንዲያገኙ በማድረግ ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት እንዲያዳብሩ ለማስቻል ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋር መስራት፣

- ለንግድና ለቱሪዝም ማስፋፋት፣ ለኢንቨስተሮች ምልመላ የሚረዱ እንዲሁም ስለአገራችን የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚዛናዊ አመለካከትን ለመፍጠር የሚያስችሉ ዶክሜንታሪ መረጃዎች በቀጣይነት ውጭ ላለው ኢትዮጵያዊ እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ በቀጥታ እንዲደርስ ለማድረግ ከማስታወቂያ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር መስራት፣

- በኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ በሬዲዮ ፋና፣ በኤፍ.ኤም 97.1 እንዲሁም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በመሠረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ አንድ አገራዊ አመለካከት ለመመሥረት በልማት፣ በሰላምና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ የሚኖረው እንድምታ በሚል ርዕስ ዙርያ የውይይት ፕሮግራም ሲካሄድ በውጭ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ እንዲዳረስ ማድረግ፣

- በዚህም ውይይት ሂደት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የሚኖራቸውን ሚና፣ ስለአገራቸው ትክክለኛ መረጃ ማግኘትና በተገቢው መልኩ ጠንካራ ትስስር መፍጠር የሚኖረው ጠቀሜታ ለሕብረተሰቡ የሚገለጽበት ሁኔታ እንዲመቻች ማድረግ፣

- የዚህ አመለካከትን የመቀየርና በአዲስ የመተካት ተግባሮቻችን scope የአጭር ጊዜ እንዳይሆን ከኢትዮጵያ የሚሌኒየም አከባበር ጋር ተሳስሮ በዚሁ ቅኘት እንዲመራ ማድረግ፣

- ለዚህ ተግባር ሁሉም አካላት ተቀናጅተው ትኩረት በመስጠት እንዲሰሩ ለማስቻል በማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚመራ የጋራ ኮሚቴ ማቋቋም፣
- የኮሚዩኒቲን እንቅስቃሴ በዝርዝር የሚያሳይ ሰፊ ሥርጭት በድረ-ገጽና በፕሬስ ማሰራጨት፣

የሚጠበቀው ውጤት:-

በመንግሥት፣ በሕብረተሰባችን፣ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን መካከል በመሠረታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ ይዘን ልማትና ዴሞክራሲን በጋራ ለመገንባት የሚያስችለን አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል::

የክንውን ጊዜ:-

ከመጋቢት - ሰኔ 1998 ዓ.ም.

3.2.4 በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን መብቶችና ጥቅሞች በአገር ቤት ከማስከበር አንፃር የሚከናወኑ ተግባራት

ዓላማ:-

መንግሥት በውጭ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ተወላጆች ለልማታችን ያላቸውን ጠቀሜታ በመገንዘብ ሁለንተናዊ ትስስሩን ለማጠናከር እንዲያግዙ ያወጣቸው ማበረታቻዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን በማስፈፀም ዙሪያ ያሉ እጥረቶችን በማረም ሙሉ በሙሉ የመብታቸው ተጠቃሚ ማድረግ፣

ግ ብ:-

መንግሥት በውጭ አገሮች ለሚኖሩ ወገኖች የሰጣቸው ማበረታቻዎች፣ አዋጆችና ደንቦች ከወቅቱ ሁኔታ ጋር እንዲቃኙ ማድረግ፣ የአፈጻጸም ችግሮችን ማስወገድ፣ ብሎም ትስስሩና ግንኙነቱ የበለጠ ውጤታማና ትርጉም ያለው እንዲሆን አድርጓል::

ዋና ዋና ተግባራት:-

- አዋጅ 270/94ን አስመልክቶ፣
  - አዋጁ በማስተካከል ከኢትዮጵያውያን ጋር በጋብቻ የተሳሰሩ የውጭ ዜጎች ሁሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
  - የትውልድ ኢትዮጵያውያን መታወቂያ አሰጣጥን ከተጠቃሚዎችና ከሚሲዮኖች በሚመጣ ሃሳብ መሰረት ላለው ችግር መፍትሄ ማዘጋጀት፣
  - ማሻሻያውን ለፈፃሚ አካላትና ተጠቃሚዎች ማስረዳትና ተግባራዊ ማድረግ ፣

የሚጠበቀው ውጤት:-

በአዋጅ 270/94 ይዘት ላይ ያለ ጉድለትና የአፈጻጸም ችግር ተሻሽሎ በዚህ ረገድ የተከሰቱ እንቅፋቶች ተወግደዋል::

የክንውን ጊዜ:-

ከየካቲት - ግንቦት/1998

- በክልሎች የሚሰጡ የመኖሪያ ቤት መገንቢያ ቦታን በተመለከተ፣
  - በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በውጭ አገሮች ተደራጅተው ቦታ የተሰጣቸው ማኅበራት የግንባታው አፈጻጸም በትክክል ስለመከናወኑ መገምገም፣ በግምገማው መነሻ ተመዝግበው ጥያቂያቸው እየታየ ላሉት በአዲስ አቅጣጫ ቦታ ማግኘት የሚችሉበትን እገዛ ማድረግ፣

- በሌሎች ከተሞች መሬት ለማግኘት ተደራጅተው ላመለከቱት ከክልሎች ጋር በመነጋገር ችግሩ የሚፈታበትና መሬት የሚያገኙበትን መንገድ ማቀላጠፍ፣
- ከትግበራው በሚገኝ ተሞክሮ በቀጣይ እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸው ከክልሎች እንዲሁም ከአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ጋር በመመካከር ወጥነት ያለው መመሪያ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣
- በሁሉም አስፈጻሚ አካላት ዘንድ የምንከተለውን የጋራ አሠራርና አቅጣጫ እንዲሁም የወጣውን መመሪያ ለሚሲዮኖች በማሳወቅ ለተጠቃሚዎች የማስረዳት ስራ እንዲከናወን ማድረግ፣
- ማኅበራቱና አባላቱ በቀጣይነት ከኤምባሲዎቻችን ጋር በመተባበር የሚጠበቅባቸውን ግዴታ እየተወጡ መሆኑን ተከታትሎ ማረጋገጥ፣

የሚጠበቀው ውጤት:-
የቤት መገንቢያ ቦታ ለማግኘት ተደራጅተው ገንዘብ ያዋጡና በየኤምባሲው የተመዘገቡ የማኅበር አባላት በተለያዩ ከተሞች መሬት በጋራ ወይም በተናጠል ያገኛሉ:: ማኅበራቱና አባላቱም ከኤምባሲዎቻችን ጋር ጠንካራ ትስስር ፈጥረው ለመንቀሳቀስ ችለዋል::

የክንውን ጊዜ:-
ከጥር - ሰኔ/1998

➢ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብትን በተመለከተ፣
  - ለተመላሽ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀውን የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት መመሪያ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በጋራ በማየት ማስተካከል፣
  - በተለይ የቤት መኪናን አስመልክቶ ለሕገ-ወጥ ነጋዴዎች መጠቀሚያ በመሆኑ እንዲሰረዝ ማድረግ፣
  - በገቢዎች ሚኒስቴር ለተመላሽ የሚሰጡ ማበረታቻዎች በኢኮኖሚው ዘርፍ ጠንካራ ትስስር በመፍጠር ራሳቸውን ጠቅመው አገራቸውን የሚጠቅሙበትን መንገድ የሚከፍትና የሚያበረታታ እንዲሆን ማድረግ፣
  - የዚህን ውሣኔ መነሻ በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በስፋት እንዲያውቁት ተጨባጭ መረጃ አዘጋጅቶ ለሚሲዮኖች መላክ፣

የሚጠበቀው ውጤት:-
በውጭ ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ለመፍጠር ተችሏል::

የክንውን ጊዜ:-
ከየካቲት - ሚያዝያ/1998

➢ በውጭ የሚኖሩ ወገኖች በአገር ውስጥ በውጭ ምንዛሪ ሂሣብ መክፈትን በተመለከተ፣

- በውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ሂሣብ በመክፈት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመመሪያው ላይ በጥናት የታየውን የተንዛዛ አሰራር ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ በሚያደርግ መንገድ ለማሻሻል ከብሔራዊ ባንክና ሌሎች ሚና ካላቸው አካላት ጋር መመካከር፣
- የተሻሻለ መመሪያ ማውጣት፣ ተጠቃሚዎች እንዲያውቀት ማድረግና መተግበር ፣

የሚጠበቀው ውጤት:-
መመሪያው ተሻሽሎ የውጭ ምንዛሪ ግኝታችን ከፍ ይላል፣ በውጭ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንን ተጠቃሚነት ተረጋግጧል።

የክንውን ወቅት:-
ከመጋቢት - ሰኔ/1998

➢ ገንዘብ ወደ አገር ውስጥ የሚተላለፍበትን ህጋዊ መንገድ ማሻሻልን በተመለከተ፣

- አሁን አገልግሎቱን እየሰጡ ካሉት የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመመካከር ክፍያው የሚቀንስበትና አገልግሎቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- አማራጭ የሃዋላ አገልግሎት ሰጪ ሕጋዊ ተቋማት የሚፈጠሩበትን መንገድ ከሚመለከታቸው የባንክና የፀጥታ አካላት ጋር በመሆን ማጥናትና ሕገወጥ የሃዋላ ተቋማትን ማክሰም፣

የሚጠበቀው ውጤት:-
ርካሽ፣ ቀልጣፋና ሰፊ አማራጮች ያለው የውጭ ምንዛሪ የሐዋላ አገልግሎት ተፈጥሯል።

የክንውን ጊዜ:-
ሚያዝያ - ሰኔ/1998

➢ የኢንቨስትመንት መስክ አመቺ እንዲሆን ማድረግን በተመለከተ፣

- ከፌዴራልና የክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ጽ/ቤቶች፣ ከተመረጡ የከተማ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት ለተከሰቱ ችግሮች ጥናታዊ ግምገማ ማድረግ፣

- ከውጭ አገር መጥተው በቀጥታም ሆነ በሽርክና የኢንቨስትመንት ሥራ ከጀመሩና ሊጀምሩ ከተዘጋጁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጋር መድረክ በመፍጠር በጋራ ምክክር መፍትሄ ማስቀመጥና የጋራ ኮሚቴ መመሥረት (በተለይ ተመላሽ ቤተ-እስራኤላውያንን በንቃት ማሳተፍ)፣
- ችግሩን የሚቀርፍ በጥናት ላይ የተመሠረተ መፍትሄ መጀመር፣ በየክልሎች ያለውን የኢንቨስትመንት ፕሮፋይልና የተወሰኑ መነሻ ጥናት የተደረገባቸውን ፕሮጀክቶች በክልሎችና በከተሞች እንዲዘጋጅ ማቀናጀት በሞዴልነት የተዘጋጁትን ለሚሲዮኖች ማሰራጨትና በአክሲዮን በጋራ የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ከውጭ አገር መጥተው በቀጥታም ሆነ በሽርክና በኢንቨስትመንት ላይ ለሚሠማሩና ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ብድር ለሚጠይቁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያለው አሠራር ተፈትሾ ቀልጣፋ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

<u>የሚጠበቀው ውጤት</u>:-
ውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በኢንቨስትመንትና በሙያቸው ለመሰማራት ያጋጠማቸው ችግር ተለይቶ እንዲሻሻል ተደርጓል።

<u>የክንውን ጊዜ</u>:-
ከመጋቢት - ሰኔ/1998

- <u>በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንን ከአገራቸው ጋር ለማስተሳሰር ለሚከናወኑ ተግባራት በአገር ውስጥ ድጋፍ ሰጪ አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋምን በተመለከተ</u>፣
  - አገር ውስጥ ተመልሰው የገቡት ተጠቃሚ በመሆን ሌላውንም ሊስቡና ማሳተፍ እንዲችሉ በቅድሚያ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ዙርያ ያሉ ችግሮች እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ጥረት ማድረግ፣
  - ከላይ የተጠቀሰውን ተግባር በመደገፍና በማምከር በቀጣይ የተቀናጀ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል መድረክ በአገር ውስጥ ለመመሥረት እንዲቻል በቅድሚያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለቤትነት አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋምና ቅድመ-ሁኔታ ማመቻቸት፣
  - በቀጣይ መድረኩን አዘጋጅቶ ኮሚቴውን መመሥረት፣ በጋራ የሚከናወኑ ተግባራትን ለይቶ ማስቀመጥና የአፈጻጸም መርሐ-ግብር ማዘጋጀት፣ መተግበርና አፈጻጸማቸውን ተከታትሎ ውጤት ማስመዝገብ፣
  - በውጭ ላሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የኮሚቴውን መመሥረት በስፋት ማስተዋወቅ፣

- በውጭ አገር ከሚገኙና ቅርበትና ትስስር ካላቸው ሚዲያዎች ጋር በመገናኘት ስለአገራቸው የማስረዳት፣ ጽሁፍ የመላክና ወደ አገራቸው መጥተው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲገነዘቡ የማግባባት ስራ እንዲሰሩ ማስተባበር፣
- ኮሚቴው በአገር ውስጥና በውጭ የጋራ አመለካከት ለመፍጠርና ለሚሲኒየም ዝግጅቱ ጭምር የሚኖረውን ሚና አሟጦ መጠቀም፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንዲተሳሰር ማድረግ፣
- በተመረጡ አገሮች የልዑካን ቡድን በሚጓዝባቸው ወቅቶች የኮሚቴው አባላት እንዲሳተፉ በማድረግ ማስማራትና የተቃዋሚ ድርጅቶችን አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ተቀባይነት እንዲያጣና እንዲከሽፍ ማድረግ፣

የሚጠበቀው <u>ውጤት</u>:-

አገር ውስጥ የገቡት ተጠቃሚ በመሆን በውጭ አገሮች የሚገኙ ወገኖችን ሊስቡና ሊያሳትፉ፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ማህበረሰብንና ሚዲያን በመቅረብ ስለአገራቸው የልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ሂደት በማስረዳት ተጨባጭ አስተዋፅኦ ማድረግ ጀምረዋል::

የክንውን ጊዜ:-

ከመጋቢት - ሰኔ/1998

# የ1998 ቀሪ ጊዜ የኮንስቲትወንሲ ግንባታ ዕቅድ የአፈፃፀም መርሐ-ግብር

## 3. በውጭ አገሮች የኮንስቲትወንሲ ግንባታን ከማሳካት አኳያ:-

### 3.1. በሚሲዮኖች የሚከናወኑ ተግባራት፣

| | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| | በውጭ አገሮች ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን መካከል ለሥርዓቱ ደጋፊ የሆኑ ሃይሎችን ለማፍራትና ለማጠናከር የሚረዳ የጥናት ሥራ ማካሄድ፣ | በውጭ አገሮች ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በቂና የወደፊት የትስስር አቅጣጫን ሊደግፍ የሚያስችል መረጃ ይኖራል፣ | በውጭ አገሮች ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በቂና የወደፊት የትስስር አቅጣጫን ሊደግፍ የሚያስችል መረጃ ሲኖር፣ | • ሚሲዮኖች ባሉበት እና በሚሸፍኗቸው አገሮች ተደራጅተው ስለሚገኙ ማህበራትና ስብስቦች ተጨባጭ መረጃ ማሰባሰብ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣ | X | X | X | | | | ሚሲዮኖች |
| | | | | • ያልተደራጁ ደጋፊና ገለልተኛ ኃይሎችን በሚመለከት ተጨባጭ መረጃ ማሰባሰብ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ፣ | | | X | X | X | | "" |
| | | | | • በጥቅሞቻቸው ዙሪያ የተሻለ የመፍትሄ አቅጣጫን የሚጠቁም ጥናት ማካሄድ፣ | X | X | X | | | | "" |
| | ከ3ኛ አገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ በውጭ አገሮች ነዋሪ የሆኑትን ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ተወላጆች በጥቂት ተቃዋሚ ኃይሎች አፍራሽ ፕሮፓጋንዳና የተለያዩ ማስፈራሪያ ስልቶች ተቋርጦ ያለውን ግንኙነትና መገለል አቅጣጫ ለመለወጥ የሚያስችል የፖለቲካ ስራ በመስራት በአገሩ የልማትና የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ላይ እምነት እንዲያሳድሩ ማድረግ፣ | በምዕራብ አውሮፓና አሜሪካ በሚገኘው ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ተወላጅ ጥቂት አክራሪ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራር አባላትና ደጋፊዎች ማንነትና አፍራሽ ተልእኮ እንዲታወቅ ይደረጋል፣ | የጥቂት አክራሪ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራር አባላትና ደጋፊዎች ማንነትና አፍራሽ ተልእኮ በምእራብ አውሮፓና አሜሪካ በሚገኘው ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ተወላጅ ሲታወቅ፣ ሲደረግ | • የአክራሪውን የተቃዋሚ ጉራ ለማዳከም እንዲረዳ ቀንደኛ አስተባባሪ የሆኑ አባላትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለዋናው መ/ቤት ማስተላለፍ፣ | X | X | X | | | | "" |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| | | | | • ከዋናው መ/ቤት በሚደርሳቸው የአነዚህ አከራሪዎች የተለያየ መረጃ/ በዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በገንዘብ ዝርፊያ፣ በመንግሥትና በሕዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት አለአግባብ ተጠቅመው የከበለሉትን፣ ወዘተ/ ለአብዛኛው የኮሚዩኒቲ አባላት ማጋለጥ የሚያስችል የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሥራት፣ | | | | X | X | X | ሚ.ሰ.ዮጥች |
| | | | | • ከእነዚህ መካከል በዘር ማጥፋትና የህዝብና የመንግሥት ንብረት በመዝረፍ የተሳተፉትን መሪ-ተዋንያን በሕግ ለመጠየቅ የሚያስችል የተጠናከረ እንቅስቃሴ በማካሄድ ተጠያቂዎቹን ለፍርድ ማቅረብ፣ | | | | X | X | X | “ |
| | | | | • አክራሪ ተቃዋሚዎች ከሚኖሩባቸው አገሮች መንግሥታት ጋር በዲፕሎማሲያዊ መስመር በመገናኘት የአገራችንን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ እንቅስቃሴዎችን በየአገሮቻቸው እንዳካሄዱ መፍቀድ እንደሌለባቸው የተለያዩ የህግ፣ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ነጥቦችን በማንሳት በጋራ መተባበር የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች መፍጠር፣ | X | X | X | X | X | X | “ |
| | የደጋፊ ኃይሎችን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚያስችሉ የፖለቲካና የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን መስራት፣ | የአገራችን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረው በውጭ ያለው ደጋፊ ሃይል ተጨባጭ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ተችሏል፣ | የአገራችንን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረው በውጭ ያለው ኃይል ተጨባጭ አስተዋጽኦ ሲያደርግ፣ | ሀ. <u>ተደራጅተው የሚገኙትን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚሰሩ ስራዎች፡-</u><br>• የወቅቱን የተቃዋሚ ኃይሎችን አፍራሽ እንቅስቃሴ በመቃወም በተለያየ መልኩ የተደራጁና የአገራችንን ትክክለኛ የፖለቲካ ገጽታ በማንፀባረቅ lobby የሚያደርጉ ግለሰቦችንና ስብስቦችን በመረጃና የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠት ማጠናከር፣ በቀጣይ ተሳትፏቸውን ሊያጉለብት የሚያስችል ዕቅድ ከነሱ ጋር በመመካከር ማውጣት፣ | | X | X | X | | | “ |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| | | | | • በአገራችን የፌዴራል የፖለቲካ ስርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ በአጋርነት የቆሙ ክልሎች ብሔር ብሔረሰብ ተወላጆችን /የሶማሌ፣ ሐረሪ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ወዘተ/ ስብስብ በመረጃ መደገፍ፣ የእንቅስቃሴ አቅጣጫዎችን በማመላከት ባሉበት አገር የትውልድ አገራቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ጥብቅና እንዲቆሙ (advocacy)ማድረግ፣ | X | X | X | | | | ሚሲዮኖች |
| | | | | • የእስከሁን አጋር ማኅበረሰብ ተሞክሮ ተጠቅሞ ደረጃ በደረጃ የሲሎች ትላልቅ ብሔር ተወላጆችን ስብስቦች በየተደራጁበት ሰስርዓቱ በጐ አመለካከት ያላቸው አመራሮችና አባላት እንዲኖራቸው የሚያስችል እገዛ በመስጠት የደጋፊ ኃይሉን መሠረት ማስፋት፣ | | | | X | X | X | ««« |
| | | | | • የተነጣጠሉና በየአገሩ የተሰራጩ አደረጃጀቶች አጋርነት ፈጥረው በከተማ፣ በክልልና በሃገር ደረጃ የጋራ አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ | X | X | X | X | X | X | |
| | | | | • የተለያዩ የልማት፣ የሙያ ማኅበራትንና ወጣቱን ትውልድ ከአገራችን ዘላቂ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ አጀንዳ አንፃር ማሰባሰብና የአገራቸውን እድገት ሲደግፉና ይህንን የሚቃወሙትንም ለመመከት እንዲችሉ ተሳትፏቸውን በመረጃና በተለያዩ ድጋፎች ማጠናከር /በስብሰባ፣ በልዩ ልዩ ሚዲያ፣ በድረ-ገጽ ወዘተ/፣ | | | X | X | X | X | ሚሲዮኖች |
| | | | | ሰ. <u>ያልተደራጁና በገለልተኝነት የቆሙትንና በተቃዋሚ ሃይሎች ተወናብደው የሚገኙትን ወደ ደጋፊነት ለማምጣት የሚሰሩ ስራዎች፡-</u> | | | | | | | |
| | | | | • በአነስተኛ አጀንዳ እና በመለስተኛ አደረጃጀት እንደፍላጐታቸው መሳተፍ እንዲችሉ የማግባባት ሥራ መሥራት፣ ማደራጀት ፣ | X | X | X | X | | | ««« |

| ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| | | | • ግልጽ መውጣት የማይፈልጉትንም በግልና በቡድን በህቡእ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማግባባትና ማሰማራት፤ | X | X | X | X | X | X | ሚሲዮኖች |
| | | | • ስራ ትስስር እና ተሰሚነት ያላቸውን የኮሚኒቲ አባላት በመጠቀም በጉ አመለካከትና ውስን ተሳትፎ የነበራቸውን በቅድሚያ ማንቀሳቀስ፤ ሴሎቹን እንዲያግባቡ ማሰማራት፤ | X | X | X | X | X | X | 〃 |
| | | | • በየአገሩ ያሉትን ደጋፊ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ ድረ-ገፆችና የሚዲያ ተቋማትን በተጨባጭ መረጃ በመደገፍ ከእነዚህም ጋር የተቀናጀ የህዝብ ግንኙነት ሥራዎችን በመስራት፤ በአመለካከት ረገድ የተገኘውን ውጤት በየጊዜው በመገምገምና የታዳሚውን አስተያየት በማሰባሰብ ቀጣይነት ባለው መልኩ መንቀሳቀስ፤ | X | X | X | X | X | X | 〃 |
| | | | • ከየአገሩ የተውጣጡ ተሰሚነት ያላቸው ኢትዮጵያውያንን እየመረጡ ወደ አገር ቤት አስመጥቶ በመመካከር ግንዛቤ ጨብጠው በመመለስ የተቀረውን ማኅበረሰብ አመለካከት እንዲቀይሩ ማሰማራት፤ ለእዚህም አመቺ መድረኮችን በየወቅቱ ማዘጋጀት፤ | | | | | X | X | 〃 |
| | | | • እነዚህን ተግባራት ለማስተባበር የሚችል የተጠናከረ መዋቅርና የአመለካከት ችግሮችን ሊያስተካክል የሚችል አሰራር በሚሲዮኖቻችን ዘንድ ፈትሾ ተግባራዊ ማድረግ፤ በየአገሩ ያለውን ማኅበረሰብ በወረዳ /district/ ደረጃ ወይም አመቺ በሆነ አወቃቀር በመከፋፈል ከኮሚዩኒቲ አባላት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ማመቻቸትና የማኅደር ማሰባሰብ ስራ መስራት (ለመነሻ ያህል የደቡብ አፍሪካን የwarden system ተሞክሮ መጠቀም)፤ | X | X | X | X | X | X | 〃 |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| 4 | በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንን ለልማት ሥራ አስተባብሮ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲያችን አጋዥ ኃይል እንዲሆኑ ማስቻል፣ | በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከመንግስታችን ጎን ተሰልፈው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እራሳቸውን ተጠቃሚ በማድረግ አገራችን ከወጪ ንግድና ከቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በቀጣይነት እያደገ የሚሄድ ጠቀሜታን ታገኛለች፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱም መጠን ትርጉም ያለው ዕድገት አሳይቷል፣ | አገራችን ከወጪ ንግድና ከኢንቨስትመንት በቀጣይነት እያደገ የሚሄድ ጠቀሜታን ስታገኝና የውጭ ምንዛሪ ግኝቱም ትርጉም ያለው ዕድገት ሲያሳይ፣ | • በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ውስጥ በጎ አመለካከትና ፍላጎት ያላቸው ለአገራችን የወጪ ምርቶች አዳዲስ ገበያ ለማስገኘት፣ ምርቶችን ለማሻሻጥ፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመመልመል፣ ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ሽርክና በመፍጠርም ሆነ ራሳቸውን ችለው በአገራቸው ኢንቨስት ለማድረግ በተጨባጭ እንዲነሳሱ መገፋፋትና ዕገዛ ማድረግ፣ | X | X | X | X | X | X | ሚሲዮኖች |
| | | | | • ከክልል መስተዳድሮች ጋር በመቀናጀት ተጨባጭ የሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፋይሎችን በማሰባሰብ ለተደራጁት ደጋፊ ማኅበራት መስጠት፣ | | | | X | X | X | "" |
| | | | | • በውጭ የተቋቋሙ የኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የንግድ ድርጅቶችና የቱሪዝም ማስፋፊያ ማዕከላትን target በማድረግ ፍላጎታቸውን ማሟላትና ችግሮቻቸውን በጋራ ለመቅረፍ መንቀሳቀስ፣ | | | | X | X | X | "" |
| | | | | • በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት በህጋዊ መንገድ የሚልኩት ገንዘብ መጠን እንዲጨምር እስካሁን ያለውን አካሄድ ገምግሞና ደካማ ጐኖችን ለይቶ መፍትሄ በማስቀመጥ የተቀላጠፈ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ | | | | X | X | X | "" |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | አስፈፃሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | • በዚህም ሂደት በአገር ቤት በውጭ ምንዛሬ የባንክ ሂሣብ ለመክፈት መሰናክል የሆኑ ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለይቶና የሌሎች አገሮችን ተጨባጭ ልምዶች ቀምሮ ከዋናው መ/ቤት ጋር በመሆን አፈጻጸሙ ውጤታማ እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፣ | | | | | X | X | ሚሲዮኖች እና ዋናው መ/ቤት |
| | | | | • በአገራችን ለሚካሄደው ልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ የሚውል ተጨማሪ resource በማስገኘቱ ረገድ አስተዋጽኦ የሚኖራቸውን ተወላጆች ለይቶ ማሳተፍ፣ | | | X | X | X | X | ሚሲዮኖች |
| | በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከሚሲዮኖቻችን ቀልጣፋ፣ ግልጽና ፍትሃዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ | በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ሚሲዮኖች በሚሰጡት አገልግሎት ረክተዋል፣ | በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ሚሲዮኖች በሚሰጡት አገልግሎት ሲረኩ፣ | • በእያንዳንዱ ሚሲዮን የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶች በQuick Wins ማሻሻያ ተፈትሸው በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ጊዜና ፍላጎት ባጣጣመ መልኩ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፣ | X | X | X | | | | ““ |
| | | | | • ለአሰራር አመቺ ያልሆኑ አገልግሎቶች ለምሳሌ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ለመውሰድና የባንክ ሂሣብ ለመክፈት በግንባር መገናኘትን የሚጠይቁ አገልግሎቶችን ወደ ተጠቃሚው ለማድረስ የተንቀሳቃሽ ቆንስላ አገልግሎትና ሌሎች አማራጮችን ፈትሾ ተግባራዊ ማድረግ፣ | | | | X | X | X | ““ |
| | | | | • በኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሱ የተለያዩ በደሎች አትም በፈቀደ መጠን ህጋዊ መስመሩን ተከትለው ተገቢውን ፍትህ እንዲያገኙ በንቃት መንቀሳቀስ/በተለይ በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ላሉ ወገኖች ትኩረት መስጠት/፣ | X | X | X | X | X | X | ““ |

## 3.2. በአገር ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት፣

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| . | በአገር ውስጥ የዴሞክራሲ ስርዓትን ለመገንባትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በሉማቱ መስክ የሚደረጉ ጥረቶችን ከመንግሥት ራዕይ፣ ተልዕኮና ግቦች አንፃር በመቃኘት አንድ አገራዊ አመለካከት ለመፍጠር የሚደረገው እንቅስቃሴ ከአገር ውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በቀጥታ እንዲደርስ ማድረግ፣ | በመንግሥት፣ በሕብረተሰባችን፣ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን መካከል በመሠረታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ ይዘን ልማትና ዴሞክራሲን በጋራ ለመገንባት የሚያስችለን አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል፣ | በመንግሥት፣ በሕብረተሰባችን፣ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን መካከል በመሠረታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ ይዘን ልማትና ዴሞክራሲን በጋራ ለመገንባት የሚያስችለን አመቺ ሁኔታ ሲፈጠር፣ | • የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የፕሮግራሞቻቸውንና የይዘ ቸውን አድማስ በማሻሻል ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በብዛት በሚኖሩባቸው የዓለም ክፍሎች በቀጥታ first hand information ከምንጩ እንዲያገኙ በማድረግ ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት እንዲያዳብሩ ለማስቻል ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋር መስራት፣ | | | | | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ማስታወቂያ ሚኒስቴር |
| | | | | • ስንግድና ስቱሪዝም ማስፋፋት፣ ስኢንቨስተሮች ምልመላ የሚረዱ እንዲሁም ስለአገራችን የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚዛናዊ አመለካከትን ለመፍጠር የሚያስችሉ ዶክሜንታሪ መረጃዎች በቀጣይነት ውጭ ላሰው ኢትዮጵያዊ እና ትውልድ ኢትዮጵያዊ በቀጥታ እንዲደርስ ለማድረግ ከማስታወቂያ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር መስራት፣ | | | | | X | X | ‹‹‹ |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| | | | | • በኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ በሬዲዮ ፋና፣ በኤፍ. ኤም 97.1 እንዲሁም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በመሠረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ አንድ አገራዊ አመለካከት ለመመሥረት በልማት፣ በሰላምና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ የሚኖረው እንድምታ በሚል ርዕስ ዙሪያ የውይይት ፕሮግራም ሲካሄድ በውጭ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊና ትውልድ ኢትዮጵያዊ እንዲደርስ ማድረግ፣ | | | | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ማስታወቂያ ሚኒስቴር |
| | | | | • በዚህም ውይይት ሂደት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የሚኖራቸውን ሚና፣ ስለአገራቸው ትክክለኛ መረጃ ማግኘትና በተገቢው መልኩ ጠንካራ ትስስር መፍጠር የሚኖረው ጠቀሜታ ለህብረተሰቡ የሚገለጽበት የሚተላለፍበት ሁኔታ እንዲመቻች ማድረግ፣ | | | | | X | X | "" |
| | | | | • የዚህ አመለካከትን የመቀየርና በአዲስ የመተካት ተግባሮቻችን scope የአጭር ጊዜ እንዲይሆን ከኢትዮጵያ የሚሌኒየም አከባበር ጋር ተሳስሮ በዚሁ ቅኝት እንዲመራ ማድረግ፣ | | | | | | | "" |
| | | | | • ለዚህ ተግባር ሁሉም አካላት ተቀናጅተው ትኩረት በመስጠት እንዲሰሩ ለማስቻል በማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚመራ የጋራ ኮሚቴ ማቋቋም፣ | | | | | | | |
| | | | | • የኮሚዩኒቲን እንቅስቃሴ በዝርዝር የሚያሳይ ሰፊ ስርጭት በድረ-ገጽና በፕሬስ ማሰራጨት፣ | | | | | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር |
| | መንግሥት በውጭ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ተወላጆች ስልማታችን ያላቸውን ጠቀሜታ በመገንዘብ ሁለንተናዊ ትስስሩን ለማጠናከር እንዲያግዙ ያወጣቸው ማበረታቻዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን በማስፈፀም ዙሪያ ያሉ እጥረቶችን በማረም ሙሉ በሙሉ የመብታቸው ተጠቃሚ ማድረግ፣ | በአዋጅ 270/94 ይዘት ላይ ያሉ ጉድለትና የአፈጻጸም ችግር ተሻሽሎ በዚህ ረገድ የተከሰቱ እንቅፋቶች ይወገዳሉ፣ | በአዋጅ 270/94 ይዘት ላይ ያሉ ጉድለትና የአፈጻጸም ችግር ተሻሽሎ በዚህ ረገድ የተከሰቱ እንቅፋቶች ሲወገዱ፣ | <u>አዋጅ 270/94ን በተመለከተ</u>:-<br>• አዋጁን በማስተካከል ከኢትዮጵያውያን ጋር በጋብቻ የተሳሰሩ የውጭ አገር ዜጎችን ሁሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ | X | X | X | | | | "" |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | • የትውልድ ኢትዮጵያውያን መታወቂያ አሰጣጥን ከተጠቃሚዎችና ከሚሲዮኖች በሚመጣ ሃሳብ መሰረት ላለው ችግር መፍትሄ ማዘጋጀት፣ | | | | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ |
| | | | | • ማሻሻያውን ለፈፃሚ አካላትና ተጠቃሚዎች ማስረዳትና ተግባራዊ ማድረግ፣ | | | | | | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር |
| | | የቤት መገንቢያ ቦታ ለማግኘት ተደራጅተው ገንዘብ ያዋጡና በየኤምባሲው የተመዘገቡ የማህበር አባላት በተለያዩ ከተሞች መሬት በጋራ ወይም በተናጠል ያገኛሉ፣ ማኅበራቱና አባላቱም ከኤምባሲዎቻችን ጋር ጠንካራ ትስስር ፈጥረው ለመንቀሳቀስ ችለዋል፣ | የቤት መገንቢያ ቦታ ለማግኘት ተደራጅተው ገንዘብ ያዋጡና በኤምባሲዎች የተመዘገቡ የማህበር አባላት በተለያዩ ከተሞች መሬት በጋራ ወይም በተናጠል ሲያገኙ፣ ማኅበራቱና አባላቱም ከኤምባሲዎቻችን ጋር ጠንካራ ትስስር ፈጥረው መንቀሳቀስ ሲችሉ፣ | <u>በክልሎች የሚሰጡ የመኖሪያ የቤት መገንቢያ ቦታን በተመለከተ</u>:-<br>• በአዲስ አበባ መስተዳድር በውጭ አገሮች ተደራጅተው ቦታ የተሰጣቸው ማኅበራት የግንባታው አፈጻጸም በትክክል ስለመከናወኑ መገምገም፣ በግምገማው መነሻ ተመዝግበው ጥያቄያቸው እየታየ ላሉት በአዲስ አትጣጫ ቦታ ማግኘት የሚችሉበትን ዕገዛ ማድረግ፣ | X | X | X | | | | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር |
| | | | | • በሌሎች ከተሞች መሬት ለማግኘት ተደራጅተው ላመለከቱ ከክልሎች ጋር በመነጋገር ችግሩ የሚፈታበትና መሬት የሚያገኙበትን መንገድ ማቀላጠፍ፣ | | | X | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና ክልሎች |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | • ከትግበራው በሚገኝ ተሞክሮ በቀጣይ እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸው ከክልሎች እንዲሁም ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ጋር በመመካከር ወጥነት ያለው መመሪያ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ | | | | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና ክልሎች |
| | | | | • በሁሉም አስፈፃሚ አካላት ዘንድ የምንከተለውን የጋራ አሰራርና አቅጣጫ እንዲሁም የወጣውን መመሪያ ለሚሲዮኖች በማሳወቅ ለተጠቃሚዎች የማስረዳት ስራ እንዲከናወን ማድረግ፣ | | | | | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር |
| | | | | • ማኅበራቱና አባላቱ በቀጣይነት ከአምባሲዎቻችን ጋር በመተባበር የሚጠበቅባቸውን ግዴታ እየተወጡ መሆኑን ተከታትሎ ማረጋገጥ፣ | | | | | | | |
| | | መመሪያው ተሻሽሎ የውጭ ምንዛሪ ግኝታችን ከፍ ይላል፣ በውጭ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተጠቃሚነት ይረጋገጣል፣ | መመሪያው ተሻሽሎ የውጭ ምንዛሪ ግኝታችን ከፍ ሲልና በውጭ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተጠቃሚነት ሲረጋገጥ፣ | <u>በውጭ የሚኖሩ ወገኖች በአገር ውስጥ በውጭ ምንዛሪ ሂሣብ መክፈትን በተመለከተ፡-</u><br>• በውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ሂሣብ በመክፈት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመመሪያው ላይ በጥናት የታየውን የተንዛዛ አሰራር ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ በሚያደርግ መንገድ ለማሻሻል ከብሔራዊ ባንክና ሌሎች ሚና ካላቸው አካላት ጋር መመካከር፣ | X | X | X | | | | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ ባንክ ፣ ንግድ ባንክ፣ UNDP፣ IOM |
| | | | | • የተሻሻለ መመሪያ ማውጣት፣ ተጠቃሚዎች እንዲያውቁት ማድረግና መተግበር፣ | | | | X | X | X | ብሔራዊ ባንክና ንግድ ባንክ |
| | | ርካሽ፣ ቀልጣፋና ሰፊ አማራጮች ያለው የውጭ ምንዛሪ የሃዋላ አገልግሎት ይፈጠራል፣ | ርካሽ ቀልጣፋና ሰፊ አማራጮች ያለው የውጭ ምንዛሪ የሃዋላ አገልግሎት ሲፈጠር፣ | <u>ገንዘብ ወደ አገር ውስጥ የሚተላለፍበትን ህጋዊ መንገድ ማሻሻልን በተመለከተ፡-</u><br>• አሁን አገልግሎቱን እየሰጡ ካሉ የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመመካከር ክፍያው የሚቀንስበትንና አገልግሎቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣ | X | X | X | | | | 〃 |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | • አማራጭ የሃዋላ አገልግሎት ሰጪ ህጋዊ ተቋማት የሚፈጠሩበትን መንገድ ከሚመለከታቸው የባንክና የፀጥታ አካላት ጋር በመሆን ማጥናትና ህገ-ወጥ የሐዋላ ተቋማትን ማክሰም፣ | X | X | X | | | | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ብሄራዊ ባንክና ደህንነት |
| | | በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በኢንቨትመንትና በሙያቸው ለመሰማራት ያጋጠማቸው ችግር ተለይቶ እንዲሻሻል ይደረጋል፣ | በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በኢንቨትመንት እና በሙያቸው ለመሰማራት ያጋጠማቸው ችግር ተለይቶ እንዲሻሻል ሲደረግ፣ | <u>የኢንቨስትመንት መስክ አመቺ እንዲሆን ማድረግን በተመለከተ፡-</u><br>• ከፌዴራልና የክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ጽ/ቤቶች፣ ከተመረጡ የከተማ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት ለተከሰቱ ችግሮች ጥናታዊ ግምገማ ማድረግ፣ | | X | X | X | | | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌደራልና ክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤቶች፣ ብሄራዊ ባንክና ደህንነት |
| | | | | • ከውጭ አገር መጥተው በቀጥታም ሆነ በሽርክና የኢንቨስትመንት ሥራ ከጀመሩና ሊጀምሩ ከተዘጋጁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጋር መድረክ በመፍጠር በጋራ ምክክር መፍትሄ ማስቀመጥና የጋራ ኮሚቴ መመሥረት፣ (በተለይ ቤተ-እስራኤላውያንን በንቃት ማሳተፍ፣) | X | X | X | | | | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን |
| | | | | • ችግሩን የሚቀርፍ በጥናት ላይ የተመሠረተ መፍትሄ መጀመር፣ በየክልሉች ያለውን የኢንቨስትመንት ፕሮፋይልና የተወሰኑ መነሻ ጥናት የተደረገባቸውን ፕሮጀክቶች በክልሉችና በከተሞች እንዲዘጋጅ ማቀናጀት፣ በሞዴልነት የተዘጋጁትን ለሚሲዮኖች ማሰራጨትና በአክሲዮን በጋራ የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ | | | | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ክልሎች |

| ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | |
| | | | • ከውጭ አገር መጥተው በተጥታም ሆነ በሽርክና በኢንቨስትመንት ላይ ለሚሠማሩና ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ብድር ለሚጠይቁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያለው አሠራር ተፈትሾ ቀልጣፋ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ | X | X | X | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ |
| | አገር ውስጥ የገቡት ተጠቃሚ በመሆን በውጭ አገሮች የሚገኙ ወገኖችን ሊስቡና ሊያሳትፉ፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ማህበረሰብንና ሚዲያን በመቅረብ ስለአገራቸው የልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ሂደት በማስረዳት ተጨባጭ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጀምራሉ፣ | ስለአገራቸው የልማትና የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ሂደት በማስረዳት ተጨባጭ አስተዋፅኦ ማድረግ ሲጀምሩ፣ | በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያንን ከአገራቸው ጋር ለማስተሳሰር ለሚከናወኑ ተግባራት በአገር ውስጥ ድጋፍ ሰጪ አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋምን በተመለከተ፡-<br>• አገር ውስጥ ተመልሰው የገቡት ተጠቃሚ በመሆን ሌላውንም ሊስቡና ማሳተፍ እንዲችሉ በቅድሚያ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ዙሪያ ያሉ ችግሮች እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ጥረት ማድረግ፣ | | | | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ተባባሪ አካላት |
| | | | • ከላይ የተጠቀሰውን ተግባር በመደገፍና በመምከር በቀጣይ የተቀናጀ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል መድረክ በአገር ውስጥ ለመመስረት እንዲቻል በቅድሚያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለቤትነት አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋምና ቅድመ-ሁኔታ ማመቻቸት፣ | | X | X | | | | ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር |
| | | | • በቀጣይ መድረኩን አዘጋጅቶ ኮሚቴውን መመሥረት፣ በጋር የሚከናወኑ ተግባራትን ተለይቶ ማስቀመጥና የአፈጻጸም መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፣ መተግበርና አፈጻጸማቸውን ተከታትሎ ውጤት ማስመዝገብ፣ | | | | X | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የጋራ ኮሚቴ |
| | | | • በውጭ ላሉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የኮሚቴውን መመሥረት በሰፊት ማስተዋወቅ፣ | | | | | X | X | "" |

| ተ.ቁ. | ተግባር | የሚጠበቀው ውጤት | የክንውን አመላካች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ | | | | | | አስተዋፅኦ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ጥ | የ | ጠ | ሚ | ግ | ሰ | |
| | | | | • በውጭ አገር ከሚገኙና ቅርበትና ትስስር ካላቸው ሚዲያዎች ጋር በመገናኘት ስለአገራቸው የማስረዳት፣ ጽሑፍ የመላክና ወደ አገራቸው መጥተው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲገነዘቡ የማግባባት ሥራ እንዲሰሩ ማስተባበር፣ | | | | | X | X | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የጋራ ኮሚቴ |
| | | | | • ኮሚቴው በአገር ውስጥና በውጭ የጋራ አመለካከት ለመፍጠርና ለሚሊኒየም ዝግጅቱ ጭምር የሚኖረውን ሚና አሟጦ መጠቀም፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንዲተሳሰር ማድረግ፣ | | | | X | X | X | "" |
| | | | | • በተመረጡ አገሮች የልዑካን ቡድን በሚንቀሳቀሱባቸው ወቅቶች የኮሚቴው አባላት እንዲሳተፉ በማድረግ ማስማራትና የተቃዋሚ ድርጅቶች አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ተቀባይነት እንዲያጣና እንዲከሽፍ ማድረግ፣ | | | | | X | X | "" |

# በውጭ አገሮች በሚገኙ ሚሲዮኖቻችን የኮንስቲትወንሲ ግንባታ የሚመራበት ማንዋል

## I. መግቢያ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፈጣን የኢኮኖሚ ልማትን፣ የዴሞክራሲ ግንባታንና ሰላምን ማረጋገጥ በከፍተኛ ኋላቀርነትና የድህነት አዘቅት ውስጥ ለምትገኘው አገራችን የህልውና ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ራዕያችንን እውን ለማድረግ የውጭ ግንኙነታችን የሚኖረውን ፋይዳ በሚገባ ያስቀመጠ አገራዊ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሚያዝያ 1996 አውጥቷል::

ይህንን ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የመ/ቤቱ የሶስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ /1997- 1999/ ተቀርጾ ዓመታዊ ዕቅዶቻችንን በዚሁ አቅጣጫ ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንገኛለን:: ከ1998-2002 ዓ.ም. የሚቆይ የአምሥት ዓመታት ስትራተጂክ ዕቅድም በቀጣይነት በመነደፍ ላይ ይገኛል::

ቀደም ሲል የተዘጋጀውን የመ/ቤቱን ስትራተጂክ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የየአመቱን ተግባሮቻችንን አፈጻጸም ለመከታተል የሚያስችል check-list ነሐሴ 1996 የተዘጋጀ ሲሆን ይኸው መመሪያ በቀጣይ ለሚኖሩ ተግባሮቻችን አፈጻጸም መከታተያ ውጤታማ የሆነ የክትትልና ድጋፍ መስጫ ማንዋል ሆኖ ይቀጥላል::

## II. የኮንስቲትወንሲ ግንባታ ዓላማና ግቦች

በውጭ አገሮች ነዋሪ የሆነው አብዛኛው ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ተወላጅ የትውልድ አገሩ አድጋና በልጽጋ የዴሞክራሲ ሥርዓቱም መሠረት ፀንቶ ለማየት ያለውን ቀና ፍላጎት ወደተጨባጭ ውጤት ለመመንዘር ኢትዮጵያዊያኑ በሚኖሩባቸው አገሮች ጠንካራ ደጋፊ ኃይል የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠይቃል::

በአገራችን ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት ለማስመዝገብና በጅምር ያሉ የዴሞክራሲ ተቋሞቻችን እንዲጠናከሩ ለማድረግ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገሮች ያሉትን የድጋፍ ምንጮች አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል::

በውጭ አገሮች ነዋሪ የሆነውን ወገናችንን በልማትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጂዎች ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡና ስለአገራቸው ሁለንተናዊ ሁኔታ ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ የጋራ አገራዊ አመለካከት ለመመስረትና በአጋርነት ተቀራርቦ ለመሥራት ወሳኝ መሠረት ነው።

ይህንን አገራዊ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ራዕይና ተልእኮ በጋራ ተሸክሞ አገራችንን ከተመጽዋችነት ለማላቀቅና በዓለምአቀፉ የውድድር መድረክ ተገቢውን ሥፍራ እንድትይዝ ለማስቻል በውጭ የሚገኙ ሚሲዮኖቻችን ተገቢውን የጋራ ይሁንታ መድረክ በማመቻቸትና ወደ ሰፊው የኮሚዩኒቲ አባል በመውረድ የግንኙነት ድልድይ ዘርግቶ የሁለትዮሽ የጋራ ግንኙነት ሰንሰለት በመመስረት እየተናበቡ መንዝን ይጠይቃል።

ከዚህ አንፃር የምንከተላቸው ዓላማ፣ ግቦችና አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. ዓላማ

1.1 በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መስክ በምናደርገው እንቅስቃሴ የኮሚዩኒቲ አባላትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣

1.2 የኮሚዩኒቲ አባላት በሚፈልጉትና በሚችሉት ደረጃ ሥርዓቱን እንዲደግፉ ማደራጀትና ማሳተፍ፣

2. ግቦች

2.1 ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥ ግቦች

ሀ. ወደ ሀገር ቤት እንደልብ እንዳይመላለሱ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮችን ማስወገድ፣

ለ. ለቤት መሥሪያ ቦታ የማግኘት ጥያቄ ያቀረቡ ግለሰቦችና ማህበራት በተለያዩ የክልል ከተሞች መሬት እንዲያገኙ አሠራሩን ማመቻቸት፣

ሐ. ንብረት በፍራንኮ ቫሉታ እንዲያስገቡ አሠራሩን ማመቻቸት፣

መ. በውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ በሀገር ውስጥ ለመክፈት ለሚያጋጥሙ እንቅፋቶች መፍትሄ ማስቀመጥ፣

ረ. በኢንቨስትመንት መስክ በሀገር ቤት ለተሠማሩና ለመጀመር ለሚፈልጉ ዕንቅፋቶችን ለይቶ በማቃለል አገልግሎቱን ፍትሃዊና ቀልጣፋ ማድረግ፣

ሰ. በአዋጅ 270/94 እና በደንቡ ዙሪያ ያሉ እጥረቶችን በማስወገድ አዋጁና ደንቡን የተሟላ እንዲሆን ማድረግ፣

## 2.2 ተሳትፎአቸውን የማስፋት ግቦች

ሀ. ውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን /ወደ አገራቸው የተመለሱትን ጭምር/ መነሻ መረጃ መያዝ፣

ለ. የሥርዓቱ ደጋፊና ገለልተኛ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የተለያዩ ስብስቦች ዓላማ፣ አደረጃጀታቸውና እንቅስቃሴያቸውን በማጥናት ወደ ተጠናከረ ተሳትፎ ማሸጋገር፣

ሐ. ያልተደራጁ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ደጋፊዎችና ገለልተኞች በምን መልክ ሊደራጁና በምን ጉዳይ ዙሪያ ሊሳተፉ እንደሚፈልጉ ማጥናትና አደራጅቶ ማሳተፍ፣

መ. ሀገር ውስጥ ተመልሰው የገቡ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ውጭ ሀገር ያሉትን በማደራጀትና በማሳተፍ እንዲያግዙ ማድረግ፣

# III. በኮንስቲትወንሲ ግንባታ ረገድ መከተል ያለብን አቅጣጫዎች

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ተወላጆችን የማሰባሰብና የማሣተፍ ተግባር የጋራ ውጤት እንዲያስመዘግብ ለማድረግ መከተል ያለብን አቅጣጫ፣

## 3.1 የኮሚኒቲ አባላት በመረጡት አጀንዳ ዙሪያ ማሰባሰብ

ሀ. ከቀላል ጉዳዮች እስከ ከፍተኛ አጀንዳ ሰፊ አማራጭ በመስጠት እንደፍላጎታቸው እንዲደራጁ ማበረታታት፣

- በሀገር ውስጥና ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ሰላም በማስፈን ጉዳዮች ዙሪያ፣
- የትውልድ ወረዳቸውን፣ ከተማቸውን፣ ክልላቸውን በልማት በማገዝ ጉዳዮች ዙሪያ /በመዋጮ፣ በሞያ ወዘተ./፣
- በተለያዩ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሞያዎች እንደየሞያቸው ተደራጅተው እንዲያግዙ በማድረግ፣
- በብሔረሰባቸው የመብትና የልማት ጉዳይ ዙሪያ፣
- የሕገ-መንግሥቱ የተወሰኑ አንቀጾች /ፌደራሊዝም፣ የግለሰብ መብት፣ የሕዝቦች መብት/ ዙሪያ፣

- የተወሰነ ፖሊሲ በመደገፍ ዙሪያ /የገጠር ልማት፣ የኢንዱስትሪ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የከተሞች ልማት ወዘተ./፣
- ሕገ-መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ በመተግበር ዙሪያ፣

3.2 የኮሚኒቲ አባላት በመረጡት የአደረጃጀት አግባብ እንዲደራጁ ማገዝ፣

- በሞያ ማህበር ወይም ቡድን፣
- በድረ-ገፅ ወይም በተለያዩ የሚዲያ ዘርፎች፣
- በዲፕሎማሲ ሥራ (lobby group)፣
- በብሔር ብሔረሰብ ማህበር /ፖለቲካዊ/፣
- በልማት ማህበር ወዘተ.

3.3 ከላይ የተጠቀሱት አደረጃጀቶችና አጀንዳዎች እንደወቅቱ ሁኔታ ሲቀያየሩ ፍላጐታቸውን መሠረት በማድረግ ማገዝ፣ ወጥ አደረጃጀትና አጀንዳ በቋሚነት ይዞ የመቀጠል አካሄድ ስለማይሰራ አጀንዳቸውና አደረጃጀታቸው እንደ ፍላጎታቸውና ወቅታዊ ሁኔታ ከቀላል ወደ ከፍተኛ እየተሸጋገረ ሲሄድና የተለያየ አማራጭ ሲይዝ ተከታትለን ማመቻቸት አለብን፡፡ ከሁኔታውና ከፍላጎታቸው ጋር የማይቀያየር ደረቅ አቅጣጫና አሠራር መከተል የለብንም፡፡

3.4 ጥቅማቸውን እያረጋገጥን ተሳትፎአቸውን ማጠናከር

- በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚኖራቸውን መብትና ጥቅም እንዲረጋገጥ ካላገዝናቸው ሥርዓቱን ሊደግፉ አይችሉም፡፡ ስለሆነም በሚኖሩበት ሀገር መብታቸው እንዲከበር፣ ወደ ሀገር ቤት እንደልብ እንዲመላለሱ፣ ንብረት እንዲያስገቡ፣ ቤት እንዲሰሩ፣ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፣ ገንዘብ በቀላሉና በርካሽ ዋጋ ወደ አገራቸው እንዲያስተላልፉ፣ ለትውልድ ኢትዮጵያዊያን የተሰጠ ሕጋዊ መብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንቅፋቶችን በየደረጃው እየፈታን ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል አለብን፡፡
- ይህን ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጥን በፍላጎታቸው በመረጡት መንገድ የተለያየ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲና የፋይናንስ ተሳትፎ በማድረግ ከአገራቸው የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ጥረት ጐን በአጋርነት እንዲሰለፉ ማደራጀት አለብን፡፡

በዚህ አብዛኛውን ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ተወላጅ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥና በፍላጐታቸው ዙሪያ የማሳተፍ ሂደት በቀጥታ ጥቅማቸውን የሚፈታተናቸው የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂዎችና ከአገራቸው ወደ ውጭ በሄዱበት ወቅት በነበረው ጊዜ ያለፈበት እውነታ ላይ ብቻ ተወስነው ከቀሩ ሕልመኞች አፍራሽ የሆነ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሲገጥመን ይችላል::

የእነዚህን ወገኖች አፍራሽ ተቃውሞ ደረጃ በመለየት ለዘብተኛ ከሆኑት ጋር መግባባት በማይችሉባቸው ጉዳዮች ላይ ላለመስማማት በመስማማት በተወሰኑ ጉዳዮች ዙሪያ ማሳተፍና ከአክራሪዎች መነጠል የሚቻልበትን ሥልቶች በመጠቀም፣ በጭፍን ጥላቻና በማንኛውም አጀንዳ ላይ አብሮ መስራት የማይፈልጉትን /zero tolerance/ በአገር ቤት ከሠሩት የዘር ማጥፋትና የሕዝብን ሃብት በመዝረፍ ከፈፀሙት ተራ ሌብነት ወንጀል ጋር በማያያዝ ማጋለጥና ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ሳያሰልሱ በቁርጠኛነት መስራት ያስፈልጋል::

በተለይ ከ3ኛው አገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ በውጭ አገሮች ነዋሪ የሆነው ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ተወላጅ የአገሩ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ጠንካራ ደጋፊ ስትራተጂያዊ አጋር እንዲሆን ከላይ በተጠቀሱት ዓላማና ግቦች እንዲሁም አቅጣጫ ዙሪያ በትኩረት ሳናንቀሳቅሰው ብንቀር ከቅርብና ከሩቅ ጠላቶቻችን ጋር በማበር ብሔራዊ ጥቅማችንን ለመጉዳትና ሥርዓቱን ለመናድ በውጭ አገሮች ፓርላማዎች፣ የአስተዳዳር አካላት፣ ሚዲያዎችና ታዋቂ ሰዎችን ዒላማ በማድረግ ለሚረባረቡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አፍራሽ እንቅስቃሴ አሳልፎ መስጠት ይሆናል::

ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር ያልሰፈነባት፣ የልማት አጋር ልትሆን የማትችልና የልማት እርዳታም የማይገባት አገር ናት የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍና ፓሊሲዎቻችንና ስትራተጂዎቻችን ላይ በቀጥታ ተጽእኖ የሚያሳድር በመሆኑ በዋናው መ/ቤትም ሆነ በሚሲዮኖቻችን ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በጋራ መንቀሳቀስና ይህን ተልእኮዎቻቸውን በማክሸፍ የአገራችንን መልካም ገፅታና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በጐ ተሞክሮዎችን በስፋት ማስተዋወቅና መሸጥ ይጠበቅብናል::

ከዚህ አንፃር ዋናው መ/ቤትና ሚሲዮኖች ከላይ የተጠቀሱትን አቅጣጫዎች ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር በማዛመድና የኮንስቲትወንሲ ግንባታ የአፈጻጸም መከታተያ በመከተል ወቅቱ የሚጠይቀውን ትኩረት ሰጥቶ በበለጠ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት በመንቀሳቀስና ተጨባጭ ውጤት በማስመዝገብ የየበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ይጠበቃል::

1. ጠንካራ constituency የመገንባት ሥራ እንደአዲስ ሀ.....ሁ ....ተብሎ የሚጀመር ሥራ ነው።

ግብ፣

እያንዳንዱ ሚሲዮን ወይም ዲኘሎማት አሁን ከሚገኝበት ዝግ ወይም ጠባብ environment ሰብሮ ወጥቷል፣ ጠንካራ የልማትና የዲሞክራሲ constituency ለመገንባት በቁጭት ተነሳስቶ የሚታይ ውጤት አስመዝግቧል።

ተግባር (1):-
እያንዳንዱ ሚሲዮን በአካባቢው የሚኖሩትን ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እንዲሁም ሌሎች የኢትዮጵያ ወዳጆች ባጠረ ጊዜ ለማወቅ የሚያስችለውን ማህደር የማሰባሰብ ሥራ ያካሂዳል።

☞ በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያንን በተመለከተ የመረጃ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉትን ዘርዝረህ አስቀምጥ፣

- ከኤምባሲው ጋር ትስስር ያላቸው የማህበረሰቡ ማህበራትና አባላት፣
- ኢትዮጵያዊያንን ያሰባሰቡ ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሙያ ማህበራት ወ.ዘ.ተ፣
- ኢትዮጵያዊያን የሚያዘወትሯቸው ወይም ያቋቋሟቸው የባህል ማዕከላት፣ መዝናኛ ቦታዎች፣ ሬስቶራንቶች፣ ወ.ዘ.ተ፣
- የውጭ ዜጎች የሚመዘገቡባቸው መ/ቤቶች፣
- ኤሌክትሮኒክ ሚዲያና ኘሬስ ወ.ዘ.ተ.

☞ ወጥነት ያለው ጥናት ለማካሄድ እንዲቻል በዋናው መ/ቤት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጉዳዮች ዋና ዳይሬክቶሬት የመመዝገቢያ ፎርም አዘጋጅቶ ለሁሉም ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ያደርጋል፣ (በ1997 ተዘጋጅቶ የነበረው የመመዝገቢያ ፎርም እንዲሻሻል ተደርጎ ይሠራበታል)።

☞ የመመዝገቢያ ፎርሙ የምዝገባው ዓላማ ለምን እንደሆነ የሚያብራራ፣ በእያንዳንዱ ሰው ሊኖር ይችላል የሚባለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ የሚረዳ ማብራሪያ የያዘ፣ አጭር፣ ቀላልና ግልፅ ሆኖ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚዘጋጅ ይሆናል፣

☞ የመመዝገቢያ ፎርሙ የሚሰራጭባቸውን ዘዴዎች እያንዳንዱ ኤምባሲ ለአካባቢው በሚስማማ መንገድ ዘርዝሮ ያስቀምጣል፣ (በአካል የሚሞላ፣ በፋክስ፣ በኤምባሲውና በኢትዮጵያዊያን ድረ-ገፆች፣ በ e-mail እና ሌሎች)፣

- የኤምባሲው አባላት በሙሉና ከኤምባሲው ውጭ በዚህ ሥራ ሊሳተፉ የሚችሉትን አሰባስቦ የሚያስማራና ማን በየትኛው አካባቢ ያሉትን እንደሚመዘግብ በግልፅ የሚያስቀምጥ ዕቅድ እያንዳንዱ ኤምባሲ ያዘጋጃል፣
- ሥራው ሁሉም የሚሳተፍበት ቢሆንም በዋናው መ/ቤት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጉዳዮች ዋና ዳይሬክቶሬት በሚሲዮኖች ደግሞ የየሚሲዮኖቹ ኃላፊዎች የሚከታተሉት ይሆናል፣
- ምዝገባው ግለሰቦችንና ቤተሰቦቻቸውን ብቻ ሳይሆን ማህበራትንና አባሎቻቸውንም ጭምር ያካትታል፣
- ከኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ውጭ ያለው የኢትዮጵያ constituency ለመመዝገብ የሚያስችል የተለየ ፎርም በዋናው መ/ቤት ተዘጋጅቶ ለሚሲዮኖች ይላካል፣ ፎርሙ ሲሞላም ለየባለአድራሻው ተልከለት የሚሞላና በሚሲዮን መሪዎች ብቻ ተልከላቸው በነሱ በኩል የሚሰበሰብ ይሆናል፣
- ምዝገባው አንዴ ብቻ ተካሂዶ የሚደመደም ሳይሆን በየ3 ወሩ ዕቅድ እየወጣለት ከዓመት ዓመት የሚቀጥል ይሆናል፣ የተገኘው ውጤትም በየ3 ወሩ ሪፖርት ይቀርብበታል::

<u>ተግባር (2)</u>:-

**ከማህበረሰቡ አባላት ጋር በግል፣ በማህበራቸው ወይም በድርጅታቸው ደረጃ መገናኘትና ፈጣን አገልግሎት ማቅረብ::**

- አድራሻ የሰጠውን የማህበረሰቡን አባል በግል ደረጃና ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ፍጠር፣
- ፈጣንና አመቺ ነው ብሎ በጠቆመህ የግንኙነት መስመር ለራሱና በአካባቢው ለሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት ይጠቅማል ብሎ የሚያየው ወይም በአንተ በኩል የታመነበት መረጃ እንዲደርሰው አድርግ፣
- ስለተላከለት መረጃም ሆነ ሌሎች የሚያነሳቸው ጥያቄዎች፣ የሚፈልገው አገልግሎት ካለ አሟላለት፣
- ግንኙነቱ ቀጣይነት እንዲኖረውና ከሁለቱም ወገን feedback የምትለዋወጡበት ሁኔታ እንዲኖር አድርግ፣
- ማህበራት ወይም ድርጅቶች ከሆኑ በአገር ውስጥ ከሚገኙ ተመሳሳይ ማህበራትና ተቋማት ጋር አገናኛቸው፣
- ይህ ዓይነቱ ግንኙነት አድራሻቸው ከታወቀ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ባጠረ ጊዜ መጀመርና መስራት ያለበት መሆኑን ተገንዝበህ ሳታቋርጥ ቀጥልበት፣

ተግባር (3):-

ግንኙነቶቹን በማስፋትና በማጠናከር የማህበረሰቡ አባላትንና የድርጅቶቹን ጥቅም ማዕከል ያደረጉና በአገራችን ልማት የሚሳተፉ ኃይሎች እንዲበራከቱ አድርግ፣

- ከዚህ በታች በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ማህበረሰብ የሚከናወን ሥራ ተብሎ በተቀመጠው መሠረት የማህበረሰቡ አባላትና ድርጅቶቻቸው በኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ከትውልድ አገራቸው ጋር እንዲመሰርቱ አድርግ:: (ለኢትዮጵያ ምርቶች ገበያ በማፈላለግ፣ ኢንቨስተር መልምሎ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት፣ በግሉም ሆነ በማህበር ተደራጅቶ ቤት በመስራት፣ በኢንቨስትመንት አቅሙ በፈቀደለት ደረጃ በመሳተፍ፣ ወ.ዘ.ተ)፣
- ቤተሰቦቹን ለማገዝም ይሁን ገንዘቡን በአገር ውስጥ ባንኮች ለማስቀመጥ የሚያስተላልፈው ገንዘብ ከፍ እንዲል አድርግ፣ ለዚህ የሚያገለግል ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት አቅርብ፣
- የማህበረሰቡ አባላትና ቤተሰቦቻቸውን የሚያሰባስቡ ማዕከላት እንዲመሰረቱ ጥረት አድርግ፣
- ተወልዶ ያደገበት መንደሩን፣ ወረዳውን፣ ክልሉን፣ አገሩን በሚመለከቱ የልማት ሥራዎች በገንዘቡም ሆነ በሙያው እንዲያግዝ አበረታታ፣
- እያንዳንዱ ኤምባሲ ለማህበረሰቡ አባላት የሚሰጠው አገልግሎት የተቀላጠፈና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን አሰራሩንና አደረጃጀቱን በ QW1 and QW2 ባጠረ ጊዜ ያስተካክል፣
- እያንዳንዱ ኤምባሲ የማህበረሰቡ አባላትና ድርጅቶቻቸው ከትውልድ አገራቸው የሚጠብቁት አገልግሎት ምን እንደሆነ አውቆ አገልግሎቱን በተሟላና ባጠረ ጊዜ ያቅርብ፣ በኤምባሲው ከሚሰጡት አገልግሎቶች ውጭ በአገር ውስጥ የሚሰጡ ከሆነ ደግሞ ከየትኞቹ ተቋማት ምን ዓይነት አገልግሎት ማግኘት እንዳለባቸው አስቀድሞ በቅንጅት እንዲፈታ/እንዲመለስ አድርግ፣
- እያንዳንዱ ኤምባሲ ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ ጋር ብሔራዊ የጋራ መግባባት ለመፍጠር በጥቂት አፍራሽ ኃይሎች የሚደረግ ሴራ እንቅፋት እንደሆነበት የማይካድ ቢሆንም፤ ዋናው ችግር ግን ዲፕሎማቱ ራሱ በቁርጠኝነት እነሱን ተጋፍጦና ለአገርና ለወገን የሚበጅ አጀንዳ እንደሌላቸው በማጋለጥ ማህበረሰቡን ለማሰባሰብ ያለመቻሉ መሆኑን ከልብ አምኖ በመቀበል፣ ፈራ-ተባ ከሚል አካሄድ ወጥቶ አስተማማኝነትና ዘላቂነት ያለው የአስተሳሰብና አሰራር ለውጥ ማምጣቱን በተግባር ያስመስክር

> *እያንዳንዱ ኤምባሲ እዚህ ላይ የተቀመጡትን የአፈፃፀም መከታተያ (check list ) ይበልጥ በመዘርዘርና ካያለበት አካባቢ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ ጠንካራ የልማት constituency መፍጠሩን በተግባር ማረጋገጥ*

እያንዳንዱ ኤምባሲ የራሱን ባለደረቦች ሙሉ አቅም ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ሊኖር የሚገባውን አጋር ኃይል በመፍጠር መጠቀም ሲገባው አሁን ባለው አካሄድ ለብቻው በኤምባሲው ተዘግቶና ከኮሚዩኒቲው ተነጥሎ ለመቀጠል ከወሰነ የልማትና ዲሞክራሲ ግንባታ ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ ይቅርና ሌሎች መለስተኛ ተግባሮችንም ለማስፈፀም ስለማይችል ኤምባሲው እንደተዘጋ በውል መገንዘብ ይኖርበታል::

2. <u>በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ የሚከናወን ሥራ</u>

ግብ:

ኤምባሲዎቻችን በያሉበት አካባቢ ጠንካራ የልማት constituency ለመገንባት በቅተዋል::

<u>ተግባር (1)</u>:-

ኤምባሲዎቻችን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያንን በያሉበት አካባቢ የትውልድ አገራቸው ጠንካራ የልማትና የዲሞክራሲ ግንባታ አጋር ወይም constituency እንዲሆኑ ለማድረግ በቁርጠኝነት ይረባረባሉ::

- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የትውልድ አገራቸው ጠንካራ አጋር ወይም constituency እንዲሆኑ የሚፈለገው ለልማትና ለኢኮኖሚ ጥቅም ተብሎ እንደሆነ፣ እነሱም ከትውልድ አገራቸው ጋር ከሚያስተሳስሯቸው በርካታ ገመዶች ውስጥ ዋናው በቀጥታም ሆነ ከቤተሰብ ጋር በተያያዘ የኢኮኖሚ ጥቅምና ትስስር መሆኑን ተረድተህ ተንቀሳቀስ፣
- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ከትውልድ አገራቸው ጋር የሚያስተሳስራቸው ዋነኛው ምክንያት ልማትና የኢኮኖሚ ጥቅም በመሆኑ እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ጠቅመው በትውልድ አገራቸው የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የጐላ ሚና እንዲኖራቸው የአገሪቱን የውጭ ንግድ በማስፋፋት፣ በአገራቸው ውስጥ ኢንቨስት በማድረግ፣ ሌሎች የውጭ ኢንቨስተሮችን በመመልመል፣ ቱሪዝምን በማሳደግ እንቅስቃሴ ሰፊና የማያቋርጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው አድርግ፣
- በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራተጂዎቻችን ልማትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን እያስገኙልን ያሉት ውጤቶችንም አቅርብ፣ የእነሱንም ጥቅም እንደሚያስጠብቁላቸው አስረዳ፣ በልማት ፖሊሲዎቹ ላይ ብሔራዊ የጋራ አመለካከት

ለመመስረት በቁርጠኝነት ስራበት፣ በዚህ ቀጣይና የተጠናከረ እንቅስቃሴህ ጠንካራ የልማት constituency እንደምትገነባ ተማምነህ ግፋበት፣

- ከላይ እስከ ታች በየደረጃው ያለው ዲፕሎማት የልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራተጂዎቻችንን ለማስጨበጥ በግልፅ መድረክ ወጥቶ የመጋፈጥ ግዴታ እንዳለበትና በተግባር እየተፈተነ አመለካከቱን ማስተካከል እንዳለበት በቁልፍ ተግባሩ በግልፅ ተቀምጧል:: የዚህ ተግባር ዓላማና ግብ ጠንካራ የልማት constituency መፍጠር መሆኑን ተረድተህ በቁርጠኝነት ግባበት፣

| |
|---|
| ልማት እውን የሚሆነው የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራተጂዎችን መሠረት በማድረግ መሆኑን ተረዳ፣ በፖሊሲና ስትራተጂ እንደዚሁም ከእነሱ በሚመነጭ ዕቅድ የማይመራ ልማት ዞሮ ዞሮ ተንገራግጮ እንደሚቆም ተገንዘብ፣ |
| በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን ለማሰባሰብ የሚካሄድ እንቅስቃሴ ልማትንና የኢኮኖሚ ጥቅምን ማዕከል ያደረገ አጋርነትና የትውልድ አገራቸውን ለመገንባት የሚያስችል እንቅስቃሴ በመሆኑ ያዝ ለቀቅ የሚደረግና በቁጥቁጥ የሚሰራ ሥራ ሳይሆን ከጥቂት አፍራሾች በስተቀር መላው ማህበረሰቡን የሚያነሳሳ ሰፊና ቀጣይነት ያለው ማዕበል መሆኑን ተረድተህ ብቃት ያለው አመራር ለመስጠት ቆርጠህ ግባበት:: |
| የፖለቲካ ሥራ የልማት ሥራ የሚሆነው፣ ለወጪ ምርቶቻችን ሰፊና አስተማማኝ ገበያ ማስገኘት፣ ኢንቨስተሮችን መልምሎ በአገራችን ኢንቨስት እንዲያደርጉ መመልመል፣ ጠንካራ constituency ገንብቶ የልማት አጋር እንዲሆኑ ማድረግ፣ ወ.ዘ.ተ የፖለቲካ ስራው ግብ ልማትን እውን ማድረግ ስለሆነ ነው፣<br>ይህን ሃቅ ተቀብለህ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጋር በልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራተጂዎቻችን ዙሪያ የጋራ አገራዊ አመለካከት ለመፍጠር ተረባረብ፣ ሁሉም ዲፕሎማቶቻችን በዚህ ተግባር እየተፈተኑ ለልማትና ዲሞክራሲ ግንባታ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያረጋግጡ:: |

<u>ተግባር (2)</u>:-

ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የአገራችንን የወጪ ንግድ በማስፋፋት እራሳቸውንና ትውልድ አገራቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲችሉ እያንዳንዱ ኤምባሲ በበጀት ዓመቱ ዕቅድና በዚህ check list በዝርዝር በተቀመጠው የወጭ ንግድን የማስፋፋት ተግባር በሰፊው እንዲሳተፉበት ያደርጋል::

- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በዋናነት እነሱ እራሳቸው የሚጠቀሙባቸው የትውልድ አገራቸው ምርቶችን ለማስመጣት ወይም በአካባቢው ሰፊ ገበያ የሚገኝላቸው የኢትዮጵያ ወጪ ምርቶችን በራሳቸው በኩል ለማስገባት ወይም ሌሎች አስመጪዎችን እንዲያግባቡ አቅሙና ችሎታ ያላቸው ሁሉ በሚያመቻቸው መንገድ እንዲሳተፉ ኤምባሲው በግልፅ መድረክ /በስብሰባ፣ በኘሬስ፣ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ፣ ወ.ዘ.ተ/ ጥሪውን ያስተላልፍ፣
- ከኤምባሲው ጋር በመተሳሰርም ይሁን በሌላ በሚያመቻቸው መንገድ ሁሉ የትውልድ አገራቸው marketing agent ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ኤምባሲው ባወጣው check list መሠረት ያስተባብራቸው፣

<u>ተግባር (3)</u>:-

**እያንዳንዱ ኤምባሲ በያለበት አካባቢ ኢንቨስተሮችን ለመመልመል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ዋናው ትኩረቱ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ላይ ያተኮረ ይሆናል::**

- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በትውልድ አገራቸው ኢንቨስት እንዲያደርጉ የቅድሚያ ትኩረት ሰጥተህ የሚጠይቁትን አገልግሎት በተቀላጠፈና ጥራት ባለው መንገድ አቅርብላቸው፣

- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ከቻሉና አቅሙ ካላቸው ለብቻቸው ካልሆነም ከውጭ በሽርክና ይዘዋቸው ከሚመጡ ባለሀብቶች ወይም ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በሽርክና ኢንቨስት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን አመቻችላቸው፣

- በዚህ check list በተቀመጠው መሠረት ከኤምባሲው ጋር በቅንጅት ወይም በሚያመቻቸው መንገድ ሁሉ በኢንቨስተሮች ምልመላ እንዲሰማሩ የሚፈልጉትን ድጋፍ ስጣቸው፣

<u>ተግባር (4)</u>:-

ኤምባሲዎቻችን ከውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የሚገኘው remittance ከፍ እንዲልና በህጋዊ የሃዋላ መንገድ እንዲልኩት ሰፊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ::

- ከማህበረሰቡ ጋር በመገናኘት ዝርዝር ጥናት አካሂድ፣
  - አሁን የሚልኩበት መንገድ (ሕጋዊ ወይም ሕጋዊ ያልሆነ)፣
  - የሚከፍሉት ክፍያ፣

- የሚያገኙት አገልግሎት፣
- አስተማማኝነቱ፣
- ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለመላክ ከኤምባሲዎቹና ከአገር ውስጥ ከሚመለከታቸው ተቋማት ሲሟላላቸው የሚፈልጉት አገልግሎት፣
- ሌሎች፣

☞ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የውጭ ምንዛሪ የባንክ አካውንት የመክፈት መብት መመሪያ መሠረት ገንዘባቸውን በትውልድ አገራቸው ባንኮች ለማስቀመጥ ያነሳሳቸዋል ወይ? እንዲሟላላቸው የሚጠይቁት አገልግሎት ምንድን ነው?

☞ የሌሎች አገሮች ኤምባሲዎች ወደየአገራቸው የሚገባውን remittance ከፍ ለማድረግ የሚሰጡት አገልግሎት (በውጭና በውስጥ) ምን እንደሆነ ማጥናት፣

☞ በሕገወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሪውን በውጭ በማስቀረት የላኪዎቹ ቤተሰቦች በአገር ውስጥ በብር እንዲከፈላቸው እያደረጉ ያሉትን ግለሰቦችና ድርጅቶች ማጥናት፣

- የግለሰቦቹ ማንነት፣
- አሰራራቸው (ባሉበት አገርም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የተሰማሩ ከሆኑ)፣
- በአገር ውስጥ የሚተባበሯቸው መሰል ተቋማት፣
- የሚያስከፍሉት ክፍያ፣
- የሚያገኙት ገቢ፣
- ሌሎች

☞ ጥናቱን መሠረት ያደረገ አማራጭ መፍትሄ አስቀምጥ፣

- በኤምባሲው የሚሰጠው አገልግሎት ምን እንደሆነ፣
- በአገር ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ምን እንደሆነ በጋራ ተመካክሮ አሰራሩን አስቀምጥ፣
- ኮሚኒቲው እንዲተማመንበት አሰራሩ በዝርዝር ታትሞ እንዲወጣ ማድረግና ኤምባሲው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ለቤተሰቦቻቸው የሚልኩት ወይም በትውልድ አገራቸው በባንክ የሚያስቀምጡት ገንዘብ ከፍ እንዲል ከኮሚኒቲዎቹ ጋር በቀጣይነት ስራ፣

ተግባር (5):-

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በያሉበት አካባቢ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚፃረር ወይም የሚጐዳ ክስተት እንዳይፈጠር ከኤምባሲዎቻችን ጋር በመተባበር የጥብቅና ሥራ (advocacy) እንዲሰሩ ያስተባብራሉ፣

- ☞ የእንቅስቃሴው ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማና ግብ እንደዚሁም ተግባራቱን በአጭሩ አስቀምጥ፣
- ☞ ከማህበረሰቡ ውስጥ በዚህ ሥራ ልምድ፣ አቅምና ብቃት አላቸው የሚባሉትን በጥናት ለይ፣
- ☞ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አግኝተህ ፈቃደኝነታቸውንና ሃሳባቸውን አሰባስብ፣
- ☞ በተደራጀ ወይም በግል ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉትን ለይተህ አስቀምጥ፣ እንደየፍላጐታቸው እንዲሰማሩ አስችል፣
- ☞ ለመንቀሳቀስ እንዲችሉ ሊሟላላቸው የሚፈልጉትን አሟላላቸው፣
- ☞ ከእንቅስቃሴው ተልዕኮ በመነሳት ዕቅዳቸውን እንዲያዘጋጁና ከኤምባሲው ጋር ሆነው እንዲያፀድቁት አድርግ፣
- ☞ በዕቅዱ ማን ምን ይሰራል፣ ግቡ ምን ይሆናል፣ መቼ ተጀምሮ መቼ ይጠቃለላል? የሚጠበቀው ውጤት ምንድን ነው? ወ.ዘ.ተ የሚሉትን የሚመልስና በተቀመጠላቸው ጊዜ እየተገመገመ ለተሻለ ውጤት እንደገና በቀጣይነት የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ፍጠር::

*በውጭ ኗሪ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የትውልድ አገራቸው ጠንካራ የልማት አጋር እንዲሆኑ ለማድረግ በምታካሂደው እንቅስቃሴ ዋናው ትኩረትህ በወጣቱ ትውልድ እንዲሆን፣ ከወጣቱም በምሁሩና በባለሃብቱ እንዲሆን አድርግ::*

3. የኢትዮጵያ ወዳጆችን ለማጠናከር የሚሰራ ሥራ

ግብ:

*ኤምባሲዎቻችን በተወከሉባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የአገራችን ወዳጆችን በማነሳሳት ለተያያዝነው የልማትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አጋር እንዲሆኑ አድርገዋል::*

<u>ተግባር:-</u>

እያንዳንዱ ኤምባሲ በተወከለበት አገር/አካባቢ የሚገኙ ነባርና አዳዲስ ወደጆችን በማግባባት የአገራችን የወጪ ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲገኝና ወደ አገራችን የሚገቡ ኢንቨስተሮችን እንዲገቡ ለመመልመልና ለልማትና ዲሞክራሲ ግንባታ እርዳታና ብድር ለማስገኘት እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል::

- ☞ በተወከልክበት አካባቢ ያሉ የሚባሉ የኢትዮጵያ ወዳጆችን /ግለሰቦች፣ ማህበራት፣ ወ.ዘ.ተ/ አስመልክቶ በዝርዝር በማጥናት በሙያ፣ ሥራ፣ ኢንተረስት፣ ወ.ዘ.ተ ለይቶ ያስቀምጣቸው፣
- ☞ የተደራጁና የቆዩ ማህበራት ከሆኑ ይበልጥ ሊያግዙህ በሚችሉበት ዘርፍ ለመንቀሳቀስ እንዲያስችላቸው በውስጣቸው የተለያዩ ቡድኖችን እንዲመሰርቱ ጥረት አድርግ፣
- ☞ ዋናው ትኩረትህ ከኢትዮጵያ ጋር የኢኮኖሚ ትስስር ካላቸው (የኢትዮጵያ ወጭ ምርት የሚያስገቡ ወይም ወደ ኢትዮጵያ ምርት የሚልኩ ወይም በኢትዮጵያ ኢንቨስት ያደረጉ) ጋር ይሁን፣
- ☞ ሁሉንም እንደየፍላጐታቸው (በግል ወይም በቡድን) አግኝተህ የሚሲዮኑ የእንቅስቃሴ ትኩረት በንግድ፣ ኢንቨስትመንትና የልማት ድጋፍ ማሰባሰብ ላይ እንደሆነ በማስረገጥ በዚህ ዙሪያ ምን ሊያግዙ እንደሚችሉ ተነጋገርበት፣
- ☞ ከዚህ ውጭ በ(lobbying and/or advocacy)፣ በጥናት፣ በሚዲያና፣ ገፅታ ግንባታ፣ ወ.ዘ.ተ ለመንቀሳቀስ ከፈለጉም ዞሮ ዞሮ የአገሪቱን የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እስካገዘ ድረስ እንዲገፉበት አድርግ፣
- ☞ በእነዚህ እንቅስቃሴዎች የሚሲዮኑንና የነሱ የሥራ ድርሻ በግልፅ ለይተህ አስቀምጥ፣ ተሳትፎአቸውን በቀጣይነት ለማስፋትና ለማጠናከር የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን ከነሱ ጋር ሆነህ አፈላልግ፣ ለተግባራዊነቱ ተንቀሳቀስ፣
- ☞ ሚሲዮኑ እንዲያሟላላቸው የሚፈልጉትን ለማሟላት ሞክር፣

- ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማና ግብ ያስቀመጠ ዕቅድ በመንደፍ ለተግባራዊነቱ እንዲንቀሳቀሱ አድርግ፣ በዚህ መልክ የማይመራ እንቅስቃሴ ውጤቱን ለመገምገም እንደማይቻል ተገንዘብ፣

- ይህ ወዳጆችን የማሰባሰብና ለልማትና ዲሞክራሲ ጠንካራ አጋር ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የማድረግ ተግባር በቀጣይነት እየሰፋና እየተጠናከረ እንዲሄድ አድርግ፣

## 4. ማ ጠ ቃ ለ ያ

የመሥሪያ ቤታችን የ1998 በጀት ዓመት ቀሪ ጊዜ መሪ ዕቅድ በመሥሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ ከሀደቀው የሦስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የተመነዘረና የወቅቱን የአገራችንን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀ መሆኑ ይታወቃል:: ይህንኑ የቀሪ ጊዜ መሪ ዕቅድ በተገቢው መንገድ ለመፈፀም እና የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ በዚህ ዝርዝር የዕቅድ አፈፃፀም መከታተያ (check-list) ላይ በተዘረዘረው መሠረት ሥራዎችን አቀናጅቶ መምራት፣ ማከናወን፣ መከታተልና ውጤቱንም ገምግሞ በወቅቱ ሪፖርት ማድረግ ይገባል::

በመሪ ዕቅዱ የተቀመጡትን ዋና ዋና ሥራዎች በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን እንዲያስችል ታስቦ የተዘጋጀው ይህ check-list የሥራዎቹን ዝርዝር ክንውን ሂደት ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም ዝርዝሩ በአፈፃፀም ወቅት ከሚያጋጥሙ ሁኔታዎች አንፃር ከቀረበው የበለጠ ተዘርዝሮ ሊዘጋጅ አይችልም ማለት አይደለም:: በመሆኑም እያንዳንዱ ፈፃሚ ክፍል በዚህ (check-list) ላይ ከሰፈሩት ዝርዝር የሥራ ሂደቶች የአካባቢው ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት የራሱን የፈጠራ (creativity) ክህሎት በመጠቀም አዳብሮ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግብ ይጠበቃል:: እያንዳንዱ ሚሲዮን ወይንም ዋናው መ/ቤት በዕቅድ ለያዛቸው ሁሉም ተግባራት በተመሳሳይ መልክ ዝርዝር የዕቅድ አፈፃፀም መከታተያ check-list እንዲዘጋጅላቸው ያደርጋል:: ከዚህም አልፎ እያንዳንዱ ሠራተኛ ለሚያስፈፅማቸው ተግባራት ሁሉ ግብና የሚጠበቀው ውጤት ተቀምጦላቸውና check-list ተዘጋጅቶላቸው የሚፈፀሙ እንዲሆኑ ያደርጋል:: ከዚህ አሰራር ውጭ የሚፈፀም ተግባር ሃብትንና ጊዜን የሚያባክን እንጂ ውጤት የሚያስገኝ አይደለም::

በመሆኑም ይህ check-list የተዘጋጀው:-

- በተለያዩ ደረጃዎች ያሉት የአመራር አካላት የሚጠበቀው ውጤት ላይ ለመድረስ የመምራት፣ የመከታተልና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነታቸውን በሚገባ እንደሚወጡና በየጊዜው ይህንን check-list በመጠቀም በሚደረገው ግምገማ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃዎች እንደሚወስዱ በማሰብ፣

- በበጀት ዓመቱ ሠራተኛው ከበላይ አመራር አካላት ብቃት ያለው አመራር እንደሚያገኝና በራሱም በኩል የሚጠበቅበትን አውቆ ያለውን አቅም አሟጦ እንደሚጠቀምና ተጨባጭ ውጤት ለማስመዝገብ በቁርጠኝነት እንደሚነሳሳ በማሰብ፣